## ምዕራፍ ሦስት

# 3. የእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት በነገረ ድኅነት ውስጥ ያለው መሠረታዊ ሚና

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ መሠረት የእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት አንዱና ዋነኛው የትምህርተ ሃይማኖት ክፍል ነው:: ከዚህም ጋር ይህ ክፍለ ትምህርት ለቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ድኅነት ትምህርት መሠረትም ነው:: የአምላክ እናት የመሆን ጸጋ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ የተሰጠ ልዩ አምላካዊ ጸጋና ክብር ነው:: ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በመርገመ ሥጋ፣ በመርገመ ነፍስ ተይዞ የነበረውን ዓለም በይቅርታውና በቸርነቱ በጎበኘ ጊዜ እንደ እመቤታችን ያለ በንጽሕና የተሸለመ፣ በቅድስና ያጌጠ ማንንም አላገኘም:: ይህንን አስመልክቶ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ሲናገር «ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአፅምኢ ዕዝነኪ:: ርስዒ ሕዝበኪ ወቤተ አቡኪ:: እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ:: እስመ ውእቱ እግዚእኪ» (መዝ. 44÷10-11) በማለት መስክሯል::

የዚህ ቃለ ትንቢት ትርጓሜ ምሥጢሩ ልጄ ሆይ÷ እዪ ተመልከቺም፤ ጆሮሽንም አዘንብለሽ ስሚ:: ባል አገባለሁ፣ በዘር በሩካቤ እወልዳለሁ ማለትን ተዪ፤ የአባትሽንም ቤት እርሺ:: ሰማያዊው ንጉሥ ክርስቶስ መዓዛ ንጽሕናሽን፣ መዓዛ ቅድስናሽን ወድዶአልና:: እርሱ ጌታሽ ነውና ማለት ነው:: በዚህ ቃለ ትንቢት መሠረት ሰማያዊውና ዘላለማዊው ንጉሥ እግዚአብሔር የእመቤታችንን ባሕርይ ለተዋሕዶ እንደወደደና ሥጋዋንም ለድኅነተ ዓለም መሣሪያነት እንደመረጠም ይመለከቷል::[92]

[92] መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 242-243:: አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 162:: ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ 380፣ 386:: Aloys Grillmeier,



የቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም ትምህርት እንደሚነግረንና እንደሚያስገነዝበን እመቤታችን ድንግል ማርያም የአምላክ እናት የመሆን ጸጋና ክብርን ያገኘችው ከሌሎቹ ሴቶች ሁሉ ልዩ በመሆኗና ተነጻጻሪም ሆነ ተወዳዳሪ በሌለው ንጽሕናዋና ቅድስናዋ ምክንያት ነው:: ይህንን በተመለከተ ስለ እርሷ ክብር የሚናገረው ቅዳሴ ሲያስረዳ «በአማን ነጸረ እግዚአብሔር እብ እምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ፤ አስተንፈሰ ወአጼነወ፣ ወኢረከበ ዘከማኪ:: ወሠምረ መዓዛ ዚአኪ፤ ወአፍቀረ ስነኪ:: ፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር» ይላል::

ይህም ማለት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በልዕልና ሆኖ አራቱንም ማዕዘናተ ዓለም በእውነት ተመለከተ፣ መረመረ:: እንደ አንቺ ንጽሕት በድንግልና፣ ሥርጉት በቅድስና፣ ክብርት በልዕልና ሆና የተገኘች ከቶ አላገኘም:: ስለዚህም መዓዛ ንጽሕናሽን፣ መዓዛ ቅድስናሽን ወደደ፤ ሥጋሽንም ለተዋሕዶ መረጠ:: ቅድመ ዓለም ያለ እናት ከባሕርዩ የወለደውን፣ በመልክ የሚመስለውንና በባሕርይ የሚተካከለውን፣ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን የሚወደውን አንድያ ልጁን ወደ አንቺ ላከ:: ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀንሽ ያደረ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔርም ጽኑዕ በአምልኮት፣ ንጹሕ እምኃጢአት፣ ልዩ እምአማልክተ ሐሰት፣ ባዕል እምንዴት፣ እኩት በአፈ ሰብእ ወመላእክት ነው» ማለት ነው::[93]

ሐዋርያዊት የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን የድኅነተ ዓለም መሠረት የሆነውን ይህንን የክርስትና እምነት ታላቅ ምሥጢር የትምህርተ ሃይማኖቷ መገለጫ በሆነውና ብሥራተ መልአክን በሚያሳዩት ቅዱሳት ሥዕላቶቿ አማካይነት ትገልጻለች::

*Christ in Christian Tradition: From the Apostolic Age to Chalcedon (451)*, 447-448. Davis, *The Seven Ecumenical Councils* (325-787): *Their History and Theology*, 244. መዝሙረ ድንግል፣ ገጽ 45-46::

[93] መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 226-227:: አባ ጽጌ ድንግል፣ «ማኅሌተ ጽጌ»፣ ገጽ 283:: አባ ስብሐት ለአብ፣ «ነግሥ፣» ገጽ 546::



ሥዕል 3:- የወላዲተ አምላክ ብሥራት

"ነጸረ አብ እምሰማይ:: ወኢረከበ ዘከማኪ:: ፈነወ ዋሕዶ ወተሰብአ እምኔኪ፤ እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ሆኖ ተመለከተ፤ እንደ አንቺ ያለ ከቶ አላገኘም:: አንድያ ልጁን ላከ፤ ከአንቺም ሰው ሆነ::"

(ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 85)

"እርሱ እግዚአብሔር አብ ንጽሕናሽን ባየ ጊዜ ስሙ ገብርኤል የሚባል ብርሃናዊ መልአኩን ወደ አንቺ ላከ:: መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፤ ኃይለ ልዑል ወልድ ሥጋሽን ይዋሐዳል አለሽ::"

(ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 126-128)



ቅድስት ድንግል ማርያም ሰማያዊውን አምላክ በማኅፀኗ ስ[illegible] ፀነሰችና ዘላለማዊውን ንጉሥ በሥጋ ስለ ወለደች እሙ ለአምላክ (የአምላክ እናት)፣ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት (የአሸናፊ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እናት) ናት:: ስለሆነም መጽሐፍ "በማኅፀንኪ ተፀውረ ብሉየ መዋዕ[illegible] ሕፃን"[94] እንዳለው ቅድመ ዓለም የነበረውና የዘመናት ጌታ የሆነው ወልደ እግዚአብሔር በማኅፀነ ድንግል ማርያም በማደሩና በኤፍራታ ቤተ ልሔም በከብቶች ግርግም ከእርሷ በመወለዱ ምክንያት እመቤ ታችን በአማን ወላዲተ አምላክ፣ በአማን ወላዲተ ቃል ትባላለች:: እመቤ ታችን እሳተ መለኮትን በማኅፀኗ ስለተሸከመች፣ ልጇ ወዳጇ መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከእርሷ በተዋሕዶ በነሣው ሥጋ መከራ በመቀበሉ፣ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ኀብስተ ሕይወት ቅዱስ ሥጋውን ስለቆረሰልን፣ ማየ ሕይወት ደሙን ስላፈሰሰልንና ቅድስት ነፍሱን ቤዛ አድርጎ ስለካሰልን የድኅነታችን ምክንያት ናት:: ከእርሷ የተገኘው መድኅን ክርስቶስም በከበረ ደሙ ፈሳሽነት ካሣ ስለከፈለልን፣ በወርቀ ደሙ ዳግመኛ ስለዋጀን፣ የክብሩ ተካፋዮችና የመንግሥቱ ወራሾችም ስላደረገን መድኃኒታችንና ሕይወታችን ነው::

ከላይ እንደገለጥነው የእመቤታችን የድንግል ማርያም ማኅፀን ለወልደ አምላክ የከበረ ዙፋን በመሆኑና የሚያቃጥለውንና ነደ እሳት የሆነ መለኮትን በመሸከሙ ሰማያውያን ከሚሆኑ ከሱራፌልና ከኪሩቤል ይልቅ እጅግ የከበረ ነው::[95] ይህንን አስመልክቶም ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ እመቤታችንን ባመሰገነበት ቅዳሴው "ፈድፋደ ብኪ ግርማ ራእይ ዘየዓቢ እምኪሩቤል እለ ብዙኃት አዕይንቲሆሙ:: ወሱራፌል እለ ፮ቱ ክነፊሆሙ" ሲል ተናግሮአል:: ምሥጢራዊ ትርጓሜውም ድንግል ሆይ ዓይኖቻ ቸው ብዙ ከሚሆኑ ከኪሩቤልና ክንፎቻቸው ስድስት ከሚሆኑ ከሱራ ፌል ይልቅ በምእመናን ዘንድ የመወደድ፤ በአጋንንት፣ በመናፍቃንና

[94] "መልክዐ ቁርባን"፣ *መጽሐፈ ሰዓታት ወመዝገበ ጸሎት፣* (አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም.)፣ ገጽ 517:: *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 153-154::

[95] አባ ጊዮርጊስ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* ገጽ 135-136፣ 254:: አባ ስብሐት ለአብ፣ "ነግሥ" ገጽ 541::

በአይሁድ ዘንድ የመፈራት እንዲሁም በሥላሴ ዘንድ የባለሟልነት ግርማ አለሽ» ማለት ነው።[96]

በመሠረቱ የእግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል እመቤታችን ሰው የመሆኑ ምሥጢር እኛን ለማዳን መሆኑ ከታወቀና ከታመነ፤ ከማኅፀነ ድንግል እስከ ቀራንዮ አደባባይ የተደረገው የድኅነተ ዓለም ጉዞ ሁሉ የተከናወነው በእርሷ ባሕርይ ስለሆነ ይህ አምላካዊ የቸርነት ሥራ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ስፍራ በጉልህ ያሳያል፣ ያስገነዝባል። በዚህም መድኅነ ዓለም ክርስቶስ በምክረ ከይሲ ተታልሎ በኃጢአት የወደቀውን፣ በፍዳና በመርገም ተይዞ የነበረውን ዓለም በሐዲስ ተፈጥሮ ያዳነውና የዋጀው ከእርሷ በተዋሕዶ በነሣው ሥጋና ደም መሆኑን ልብ ይሏል።[97]

ይህም ይታወቅ ዘንድ መፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር በጥንተ ተፈጥሮ በዕለተ ዓርብ የፈጠረውን የሰው ልጅ ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ እንደፈጠረው (እንዳዳነው) ሲያጠይቅ በዕለተ ዓርብ ተሰቀለ። ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ይህንን አማናዊ የድኅነት ምሥጢር ሲገልጽ «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉ አዲስ ሆኖአል» (2ኛ ቆሮ. 5÷17) በማለት አስረግጦ ተናግሮአል።

በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምናነበው ሦስተኛው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተብሎ በሚጠራው በጉባኤ ኤፌሶን የተረቀቀውና የተወሰነው የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ እመቤታችን «ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም» ተብላ እንድትጠራ ይደነግጋል። ይህ ሃይማኖታዊ ውሳኔ የቤተ ክርስቲያናችንን

[96] መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 226-227። Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology*,140.

[97] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 138፣ 187፣ 213፣ 215-216። ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 226። Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology*, 151.



የነገረ ማርያም ዶግማ [Marian Dogma / Marian Theology] ስፋትና ጥልቀት፣ ርቀትና ምጥቀት እንዲኖረው ከማድረጉም በላይ ቀደም ሲል በጉባኤ ኒቅያ የተወሰነውንና «መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፤ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የተካከለ የባሕርይ አምላክ ነው» የሚለውን የነገረ ሥጋዌ አማናዊ ትምህርትና ትክክለኛ ምስክርነት [Christological Teaching / Christological Assertion] የሚያጸና ኦርቶዶክሳዊ ቃለ ሃይማኖት ነው።[98]

ከዚህም ጋር ጉባኤ ኤፌሶን በወቅቱ የነበረውንና እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ ሰብእ *[Anthropotokos]* እንጂ ወላዲተ አምላክ › *[Θέοτοκος - Theotokos]* አይደለችም የሚለውን ንስጥሮሳዊ የክሕደት አረም ነቃቅሎ ጥሎ በትንቢተ ነቢያትና በስብከተ ሐዋርያት የተነገረውን አማናዊ ቃለ ሃይማኖት መሠረት ያደረገ ቀጥተኛና ትክክለኛ የነገረ ማርያምንና የነገረ ሥጋዌን ትምህርት በመስበኩ ይህ ጉባኤ በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ «ኦርቶዶክሳዊው ዓለት» ["The Rock of Orthodoxy"] በመባል ይታወቃል።[99]

## 3.1 የዐሥራው መጻሕፍት ምስክርነት

እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአማን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ፣ በአማን ወላዲተ ቃል መሆኗን በስፋትና በግልጥ ይመሰክራሉ። ይህም አማናዊ የቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የድኅነተ ዓለምን ተስፋ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰጠበትና «ናሁ እግዚአብሔር አዳም ኮነ ከመ አሐዱ እምኔነ፤ እግዚአብሔር አምላክም አለ:- እነሆ አዳም ... ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» (ዘፍ. 3÷22) ተብሎ በቅድስት ኦሪት በተነገረው አምላካዊ ቃለ ትንቢት ይጀምራል። ስለሆነም ይህ

[98] Gaventa, *Mary: Glimpses of the Mother of God*, 12. Mascall, "The Mother of God," 93.

[99] Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology*, 329. Ware, *The Orthodox Church*, 25, 28, 258.

የድኅነት ተስፋ ወልደ እግዚአብሔር በተለየ አካሉ ወለተ አዳም ከሆነችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው ሆኖ በተወለደ ጊዜ ፍጻሜውን አግኝቷል::(100)

ከዚህም ጋር "አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" የሚለው አምላካዊ ቃል ከእመቤታችን በተዋሕዶ ሰው ሆኖ የተወለደው መድኅን ከሦስቱ አካላት ማለትም ከቅድስት ሥላሴ አንዱ ወልድ መሆኑን በግልጥ ያሳያል:: ይህ ደግሞ በአንጻሩ እግዚእ ለአዳም፣ አምላክ ለአዳም የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ የወለደች እመቤታችን እሙ ለአምላክ፣ ወላዲተ አምላክ መሆኗንም ይመሰክራል:: በዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ የሰው ልጆች ድኅነት የመለኮታዊ ክብር ተካፋይ ለመሆን ከመቻልና ከመብቃት [Divinization / Deification] ጋር የሚገናዘብ መሆኑን በአጽንኦት ይገልጻል::

በመሆኑም ይህ የድኅነት ጸጋ በወላዲተ አምላክ በኩል በተከናወነው ረቂቅና ድንቅ የሥጋዌ ምሥጢር አማካይነት መፈጸሙ ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን መሠረታዊ ሚና በጉላ በተረዳ መልኩ ያስገነዝበናል:: በዚህ የተዋሕዶ ምሥጢርም ከቅድስት ሥላሴ አንዱ ወልድ ወለተ አዳም (የአዳም ልጅ) የምትሆን የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋ በተዋሕዶ በመንሣቱ ምክንያት የአዳም ሥጋ ከቅድስት ሥላሴ አንዱ ወልደ እግዚአብሔርን ሆነ::

ይህንን ድንቅ ምሥጢር አስመልክቶ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር "አሐዱ ዘእምቅድስት ሥላሴ ርእዮ ትሕትናነ አጽንነ ሰማየ ሰማያት፤ ወጽአ ወኃደረ ውስተ ከርሠ ድንግል፤ ከሦስቱ አካላት ማለትም ከቅድስት ሥላሴ አንዱ ወልድ በመንጸፈ ደይን መውደቃችንን፣ በእግረ አጋንንት መጠቅጠቃችንን አይቶ ባሕርዩን ዝቅ አድርጐ ከልዕልና

(100) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia,* 26-28. Meersseman trans. *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God,* 31.



ወደ ትሕትና ወረደ፤ በድንግል ማርያም ማኅፀንም ተወሰነ:: ማኅፀኗንም ዓለም አድርጐ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን አደረ" ብሏል:: በመቀጠልም ይኸው ሊቅ "ወኮነ ሱብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ፤ ወተወልደ በቤተ ልሔም በከመ ሰበኩ ነቢያት አድኃነነ ወቤዘወነ ወረሰየነ ሕዝበ ዚአሁ"(101) ዳግመኛም ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ማኅደረ መለኮት ወመዝገበ ቃል ከሆነችው ከድንግል ማርያም ተወልዶ ከኃጢአት ብቻ በቀር እንደ እኛ ፍጹም ሰው ሆነ:: ዐበይት ነቢያት፣ ደቂቀ ነቢያት በመንፈስ ትንቢት ተመርተው በተለያየ ኅብረ አምሳል እንደመሰሉለትና በብዙ ዓይነት ኅብረ ትንቢትም እንደተናገሩለት መጠን በኤፍራታ ቤተ ልሔም ተወለደ:: በዚህ ረቂቅና ድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶም ከሞት አዳነን፣ ከፍዳና ከመርገም ዋጀን፣ ለርስቱ የተለየና ለመንግሥቱም የተመረጠ ልጆቹ ወገኖቹም አደረገን ሲል ምሥጢሩን አብራርቶና አፍታቶ ተናግሮአል::

ከላይ የገለጥነው አምላካዊ የድኅነት ተስፋ ፍጻሜም በወንጌለ ቅዱስ ዮሐንስ ተብራርቶ ተጠቅሷል:: ይህንን አስመልክቶም ወንጌላዊው ሲናገር "ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ" (ዮሐ. 1÷14) ብሏል:: ይህም ኃይለ ቃል አስቀድሞ "አዳም ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ" (ዘፍ. 3÷22) ተብሎ በቅድስት ኦሪት የተነገረው አምላካዊ የቸርነት ቃል ፍጻሜ መሆኑን ይመሰክቷል:: ስለሆነም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ አምላከ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ በወለተ አዳም በቅድስት ማርያም ማኅፀን በማደሩና በእርሷ ባሕርይ በመወለዱ ዳግማዊ አዳም [Second Adam] መባልን ገንዘብ አድርጓል:: ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም "ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜም ወደ ነገሥተ ገሊላ ቤተ መንግሥት አልገባም፤ በወለተ ሄሮድስ ንጉሥም አላደረም:: ይልቁንም ከፍጹም ትሕትናው የተነሣ በቤተ ዮሴፍ በነበረች በድንግል ማኅፀን አደረ እንጂ"(102) በማለት መስክሮአል::

(101) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ 144-145::

(102) አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ [Abba Giyorgis Di Sagla]፣ *መጽሐፈ ምሥጢር*፣ *["Il Libro Del Mistero"]* ፣ ገጽ 6::

ይህንን አምላካዊ ቸርነት በተመለከተ ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ "ፈትል ነዊኅ ዘኢተበትከ እምአብ፤ ፈጣሬ ሰማያት ወምድር እምሰማያት ወረድከ በፈቃድከ፤ ማኅፀነ ድንግል አግመረተከ፤ ንስቲት ወሰተ ወሰትሙ ሰነዳያን ፃ ፈተከ፤ ገሊባዊት ሐቀፈተከ፤ አፅናዕካ ወአደንገፀት ብከ፤[103] ከአብ የማይለይ ረጅም ፈትል፤ ፈጣሬ ዓለማት፣ እምዓኤ ዓለማት ወመጋቤ ፍጥረታት የሆንክ አምላክ የሰው ልጆችን ለማዳን ስትል በፈቃድህ ከልዕልና ወደ ትሕትና መጣህ:: የድንግል ማኅፀን ወሰነህ፤ ተሸከመህም:: ከቅዱስ ኢያቄምና ከቅድስት ሐና  የተወለደች የአሥራ አምስት ዓመት ብላቴና ድንግልም ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀኗ ተሸከመችህ:: ገሊላዊት የምትሆን እመቤታችን የማትጨበጥና የማትዳሰስ አንተን በክንዶቿ ታቀፈችህ፣ በንጽሕና በቅድስና፣ በእናትነትና በድንግልናም አጸናሃት፤ በአንተም አልደነገጠችም" በማለት  አስተምሮአል::

ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ የተሰኘው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም "መጽሐፈ ምሥጢር" በተሰኘው ድርሰቱ ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶ ሲገልጽ አረጋዊው ጻድቅ ቅዱስ ዮሴፍ ከሰው ኅሊና፣ ከመላእክት አእምሮ በላይ ረቂቅ የሆነውን የሥጋዌ ምሥጢር በማድነቅ እመቤታችንን "እምኀበ መኑ ኮነ ዝፅንስ:: አንሰ እምአመ ተወፈይኩኪ ኢተሐበልኩ ለቀፈቦትኪ፣ ይህ ፅንስ ከማን ሆነ፣ ተገኘ፣ ተደረገ? እኔ ከእደ መንፈስ ቅዱስና ከእደ ካህናት በተቀበልኩሽ ጊዜ አንቺን ለመቅረብ አልደፈርኩም" ሲል እንደጠየቃት ይናገራል:: ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምም ለቅዱስ ዮሴፍ ስትመልስለት "አንሰ ኢርኢኩ አባሁ ለዘተፀንሰ በከርሥየ፤ ወኢነጸርኩ ገጾ ለዘተጸውረ በማኅፀንየ:: አንሰ ኢቀረብኩ ኀበ ብእሲ አላ ኃይል ኅቡእ ዘኢያስተርኢ ኃደረ ወተፀውረ ውስተ ማኅፀነ ሙላድ ዘእንቲአየ" ብላለች:: የዚህ ቃለ አውሥኦ ትርጓሜም በማኅፀኔ የተፀነሰውን የአካላዊ ቃል የእግዚአብሔር ወልድን ሥጋዊ (ምድራዊ) አባቱን ፈጽሞ አላየሁም:: በማኅፀኔ ያደረውን የወልደ እግዚአብሔር ፊቱንም

(103) *መጽሐፈ ቅዳሴ*፣ ገጽ 392-393:: ቅዱስ ቄርሎስ፣ "ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ"፣ *ሃይማኖተ አበው*፣ ምዕ. 78፣ ክፍል 48 (አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1986 ዓ.ም.)፣ ገጽ 304-306::



አልተመለከትኩም:: ዳግመኛም ወደ ወንድ አልቀረብኩም፤ ይልቁንም የማይታይና የማይመረመር ረቂቅ ቃል በማኅፀኔ ተቀረጸ እንጂ"[104] ማለት ነው::

ቅድስት ድንግል እመቤታችን "በማኅፀኔ ያደረውን የወልደ እግዚአብሔር ፊቱን አልተመለከትኩም" ስትል የመለሰችው ኃይለ ቃል አስቀድሞ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ለወዳጁ ለሙሴ ከነገረው አምላካዊ ቃል ጋር ይገናዘባል:: ይኸውም ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከባለሟልነቱ የተነሣ ከዕለታት አንድ ቀን አምላኩ እግዚአብሔርን "እባክህ ክብርህን አሳየኝ" ሲል በትሕትና ሆኖ ጠይቋል:: ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔርም ለሙሴ ሲመልስለት "ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም... ጀርባዬንም ታያለህ፤ ፊቴ ግን አይታይም::" (ዘጸ. 33÷18-23) ብሎታል:: እንግዲህ ከዚህ አምላካዊ ቃል የምንረዳው ከፍጡራን ወገን እግዚአብሔርን በመለኮታዊ ክብሩና በአምላካዊ ባሕርዩ ፈጽሞና ጠንቅቆ ማየትና መረዳት የሚቻለው አንዳችም ፍጡር አለመኖሩን ነው:: ከዚህም ጋር ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድያ ልጁ እርሱ ተረከው::" (ዮሐ. 1÷18) በማለት በአጽንኦተ ቃል መስክሮአል::

ይሁን እንጂ መፍቀሬ ሰብእ የሆነው እግዚአብሔር ለባለሟሉ ለሙሴ ፊቱን ሳይሆን ጀርባውን እንደሚያይ አምላካዊ ተስፋ ሰጥቶታል:: የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ሊቃውንት እንዳመሰጠሩት ይህ አምላካዊ ተስፋ በኋለኛው ዘመን አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ለድኅነተ ዓለም ቤዛ መሥዋዕት ሲሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ በእኛ ባሕርይ በተገለጠ ጊዜ ሊቀ ነቢያት ሙሴ በታቦር ተራራ ብርሃነ መለኮቱንና ምሥጢረ መንግሥቱን እንደሚያይ

(104) አባ ጊዮርጊስ [Abba Giyorgis], "*መጽሐፈ ምሥጢር*" *["The Book of Mystery"]*, ገጽ 6-7:: *መጽሐፈ ልደታ፣* *["The Book of the Nativity of St. Mary"]*, ed. M. Chaine, *CSCO*, vol. 7, *Scriptores Aethiopici*, 10-13. Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 45-46.

የሚያስረዳ ኃይለ ቃል ነው:: በቅዱስ ወንጌል እንደተገለጸው ይህ
ቃለ ተስፋ በዘመነ ሥጋዌ በደብረ ታቦር እንደተፈጸመ ልብ ይሏል::[105]
(ማቴ. 17÷ 1-8፤ ማር. 9÷2-8፤ ሉቃ. 9÷28-36)

የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት ከሣቴ
ምሥጢር የሆነው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከመድኅነ ዓለም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት በቅድስት ኤልሳቤጥ አድሮ በግልጥ
መስክሮአል:: ይኸውም በወንጌለ ቅዱስ ሉቃስ እንደተጻፈው ቅድስት
ድንግል እመቤታችን ኤልሳቤጥን በጎበኘቻት ጊዜ ቅድስት ኤልሳቤጥ
መንፈስ ቅዱስን ተመልታለች:: ኤልሳቤጥም በዚህ ጸጋ መንፈስ
ቅዱስ ተቃኝታና ድምጿን ከፍ አድርጋ "አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተ
ሽ የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው" (ሉቃ. 1÷39-43)
ስትል ወላዲተ አምላክን አመስግናለች:: በዚህም ቃለ ውዳሴ ፍሬ
ማኅፀኗ ኢየሱስ ክርስቶስ መርገመ ሥጋን፣ መርገመ ነፍስን የሚያ
ርቅ፤ በረከተ ሥጋ፣ በረከተ ነፍስን የሚያድል ቡሩክ አምላክ መሆኑን
መንፈስ ቅዱስ ስላስረዳ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን
እመቤታችንን እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ብላ ታምናለች:: ይህንን
አስመልክቶ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር "ሕፅነ ድንግል ማር
ያም ማለትም የእመቤታችን እቅፍ አምላከ እስራኤል እግዚአብሔር በ
ረድኤት የሚያድርበትን፣ በዓምደ ደመና የሚወርድበትንና የሚገለጥበ
ትን የሲና ተራራን ይመስላል:: (ዘጸ. 19÷16-20) ይኸውም ለሁሉ
የሚደንቅ ምሥጢር አለው:: የሲና ተራራ የደነገጠና የፈራ ሲሆን ሕፅነ
ድንግል ማርያም ግን ይህ ሁሉ አላገኘውም"[106] በማለት በአን
ክሮ ተናግሮአል::

ወደፊት በምዕራፍ አምስት በስፋት እንደምናየው በኢትዮጵ
ያውያን ሊቃውንት የተደረሰውና በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስ

---

(105) *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 178-179:: Brock, *Bride of Light,* 141-142. ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ፣* ገጽ 225፣ 378::

(106) Brock, *Bride of Light,* 98.



ቲያናችን በስፋት የሚታወቀው "መልክዐ ማርያም" የተሰኘው የእመቤ
ታችን ምስጋና መቅደሰ እግዚአብሔር ለመሆን የበቃውን ቅዱስ
አካሏንና የተለያዩ ሕዋሳቷን በመዘርዘር እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ
የመሆኗን ምሥጢር ይገልጣል:: ከዚህም ጋር ቅዱሳን የወላዲተ
አምላክን ሕዋሳት አማላጅ እያደረጉ ፈጣሪያቸውን ተማጽነዋል::

ለምሳሌ ያህል የመልክዐ ማርያም ድርሰት በቅድስናና በንጽሕና
የከበረውን ሁለንተናዊ የእመቤታችን ሕይወት ማለትም እሳተ መለኮ
ትን የተሸከመ ማኅፀኗን፣ የድንግልና ወተትን እያጠቡ መድኅነ ዓለም
ኢየሱስ ክርስቶስን ያሳደጉ ጡቶቿን፣ በተአምኖተ እግዚአብሔር የጸና
ውንና በፍጹም ትሕትና የተሞላ ልቡናዋን፣ ሥጋዊ ነገርን ከማሰብ
በመንፈስ ቅዱስ የተደነገለውን (የተጠበቀውን) ኅሊናዋን፣ ልጇ ወዳጇ
ኢየሱስ ክርስቶስን የታቀፉ ክንዶቿንና የዳሰሱ እጆቿን፣ ወደ ምድ
ረ ግብጽ የገሰገሱ እግሮቿን፣ ሰማያዊውን ንጉሥ የተሸከመ ጀርባዋን፣
ቅዱሳን መላእክትና ደቂቀ አዳም ያላዩትን ልዩ አምላካዊ ምሥጢር
ለማየት የተመረጡ ዓይኖቿን፣ ከመልአከ ብሥራት ከቅዱስ ገብርኤል
አንደበት ቃለ ውዳሴንና ዜና ብሥራትን የሰሙ ጆሮዎቿን፣ እንዲሁም
የድኅነተ ዓለም ተስፋ በምሥጢረ ተዋሕዶ አማካይነት እንዲፈጸም
ምክንያት የሆነውን የእምነት ቃሏን የተናገረችበትና በጎ ፈቃዷን
የገለጠችበት አንደበቷን ወ.ዘ.ተ. በመዘርዘር ተገቢውን ክብርና ምስጋና
ያቀርብላታል::[107]

መልክዐ መልክዕ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ
ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ዘንድ በሰፊው የታወቀና የሚሠራበት
የጸሎትና የምስጋና ድርሰት ነው:: መልክዕ የሚለው ቃል በቁሙ ሲተ
ረጐም ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ያለውን የአንድን ሰው
ውሳጣዊ አካልና አፍአዊ አካል ወይም ደግሞ ሁለንተናዊ ሰውነትን

---

(107) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia,* 89: ዐቢ ዘርዐ ያዕቆብና ዐቢ ናዖድ፣ "መልክዐ ማርያም"፣ *መዝሙረ ዳዊት ወመዝገበ ጸሎት፣* (አሥመራ፤ ኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም.)፣ ገጽ 521-535::

ያጠቃልላል::: በምሥጢራዊ ትርጓሜው ደግሞ የቅድስት ሥላሴን፣ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን፣ የወላዲተ አምላክ የድንግል ማርያምን፣ የቅዱሳን መላእክትን፣ እንዲሁም የቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕ ታትን ምስጋና በየደረጃው ቀምሮ የያዘ የምስጋና መድበል ነው:: በቤተ ክርስቲያናችን በስፋት የሚታወቀው የመልክዐ መልክዕ ምስጋና አገር በቀል የሆኑ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የደረሱት ቃለ ውዳሴ ነው:: ስለሆነም ይህ ዓይነቱ ልዩ ጣዕመ ውዳሴ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት ልዩ ከሚያደርጉት ምሥጢራዊ ድርሰቶች አንዱና ዋነኛው ነው::(108)

የመልክዐ ማርያም ድርሰት ሰፊና ጥልቅ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ልዩ ምስጋና ነው:: ለምሳሌ ያህል ብንመለከት መምህረ ቅዱሳን የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር «የእናንተ ግን ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ ጆሮዎ ቻችሁም ስለሚሰሙ ብፁዓን ናቸው» (ማቴ. 13÷16) በማለት ቅዱሳን ሐዋርያትን አመስግኗቸዋል:: ከዚህም ሌላ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎ ስ «መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው እንዴት ያማሩ ናቸው» (ሮሜ 10÷15) ሲል ወልደ እግዚአብሔር እንደ ነገሠ፣ ዲያብ ሎስ እንደተሻረ፤ መርገመ ሥጋ፣ መርገመ ነፍስ እንደጠፋ፤ ድኅነተ ሥጋ፣ ድኅነተ ነፍስ እንደተገኘ የምትናገረውን ሕገ ትሩፋት ወንጌልን በሁሉ ለሁሉ ለማዳረስ የሚፋጠኑ እግሮች ንዑዳን፣ ክቡራን መሆናቸውን በአጽንኦት መስክሮአል::

በዚህ መሠረት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ በጉባኤ ሲያስተምር ከሕዝቡ መካከል በጣዕመ ስብከቱ የተ መሰጠችና የረካች፣ ልቡናዋም በቃሉ የተነካ አንዲት ሴት ድምፇን ከፍ አድርጋ፡- «ብፅዕት ከርሥ እንተ ፆረተከ፤ ወብፁዓት አጥባት እለ ሐፀናከ፤ አንተን

(108) ሀብተ ማርያም ወርቅነህ (ሊቀ ሥልጣናት)፣ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህ ርት*፣ ገጽ 53-55:: ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፣ ገጽ 566::



ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የተሸከመች ማኅፀን ብፅዕት ናት:: የድንግልና ወተትን እያጠቡ ያሳደጉህ ጡቶችም ብፁዓን፣ ንዑዳንና ክቡራን ናቸው::» (ሉቃ. 11÷27) ስትል ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማር ያምን አስመስግናታለች:: ይህም ቃለ ውዳሴ «የወንጌል መልክዐ ማር ያም» ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም::

ስለዚህም ከላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ መሠ ረት በማድረግ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በመልክዐ ማርያም ምስጋናቸው መጠነ ሰፊ የሆነውን የእመቤታችንን ቃለ ውዳሴ ደርሰውላታል:: ይህ የእመቤታችን ምስጋና ስልሳ አራት አንቀጾችን የያዘ ሲሆን ምሥጢሩም ቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያም በዚህ ዓለም የኖረችበትን ዕድሜ ወይም በዐጸደ ሥጋ የቆየችባቸውን ስልሳ አራት ዓመታት /የእንግድነት ዘመናቶቿን/ ያመለክታል:: (1ኛ ጴጥ. 1÷17)

ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እንደተረጐሙት በዘመነ ብሉይ የነበሩ ቅዱሳን አበውና ቅዱሳን ነቢያት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በዘዐምሔተ አምሳል ወትንቢት (በምሳሌና በትንቢት መነጽር) አይተዋታል:: በመንፈሰ እግዚአብሔር ተቃኝተው፣ በቅብዐ ትንቢት ከብረው የመሰከሩት እነዚህ ነቢያት እመቤታችን ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን ከገለጡባቸው አያሌ ምሳሌዎችና ትንቢቶች መካከል፡- ዕፀ ጳጦስ ዘሲና (ሙሴ በደብረ ሲና ያያት ዕፅ)፣ ልዑለ ቃል ኢሳይያስ «ናሁ ድንግል ትፀንስ፣ ወትወልድ ወልደ፣ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ እግዚአብሔር ወልድን በድንግልና ትወልዳ ለች፣ ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች» ሲል ስለ አማኑኤል የተናገረው ቃለ ትንቢት፣ ነቢየ አምላክ ዳንኤል ያየው ረጅም ተራራ፣ እንዲሁም ነቢየ እግዚአብሔር ሚክያስ ስለ ኤፍራታ ቤተ ልሔም የመሰከረው ትንቢታዊ ቃለ ተስፋ ናቸው::

## 3.1.1 ዕፀ ጳጦስ ዘሲና

ሊቀ ነቢያት ሙሴ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት በአምሳለ ነበልባል ወሐመልማል አይቶአል:: (ዘጸ. 3÷1-10) ሙሴ በደብረ ሲና እንደተመለከተው ነበልባሉ በእሳትነቱ ሐመልማሏን ሳያቃጥላት፣ ሐመልማሏ ደግሞ በእርጥብነቷ ነበልባሉን ሳታጠፋው ፍጹም ተዋሕደው መገለጣቸው ምሥጢሩ በኋለኛው ዘመን አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም እንበለ ውላጤ (ያለ መለወጥ)፣ እንበለ ቱሳሔ (ያለ መቀላቀል)፣ እንበለ ትድምርት (ያለ መጨመር)፣ እንበለ ቡዓዴ (ያለ መደረብ) እንዲሁም ያለ መጣፋት በተዋሕዶ ሰው እንደሚሆን የሚያስረዳ ነው:: ስለሆነም ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስና ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በሲና ተራራ ለሙሴ የታየው ነበልባል የመለኮት /የጌታ/፣ ሐመልማል ደግሞ የትስብእት /የእመቤታችን/ ምሳሌ መሆኑን በሚገባ ገልጸው ተናግረዋል:: ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በሲና ሐመልማል መመሰሏም እሳተ መለኮትን በማኅፀኗ በተሸከመች ጊዜ እሳትነቱ ስላላቃጠላት ነው::(109)

ይህንን ታላቅና ድንቅ ምሥጢረ ተዋሕዶ አስመልክቶ ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር:- "እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሊቀ ነቢያት ሙሴ በነደ እሳት ተከባ ቅጠሏ ሳይቃጠሉ በደብረ ሲና ያያት ዕፀ ጳጦስን ትመስላለች" ብሏል:: ምክንያቱም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከሥጋዋ ሥጋን፣ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ከእርሷ ሰው ሆኗልና" ነው::

ዳግመኛም "አካላዊ ቃል ከእርሷ ሰው ሲሆን ባሕርየ መለኮቱ አልለወጣትምና ወላዲተ አምላክ ሙሴ በደብረ ሲና ያያት ዕፅን

(109) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 50-52:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 171፣ 379:: ቅዱስ ያሬድ፣ *ዝማሬ መዋሥዕት*፣ ገጽ 125:: Brock, *Bride of Light*, 64, 141.



ትመስላለች" አለ:: እርሱም ከእርሷ ሰው ሲሆን ባሕርየ መለኮቱ አልተለወጠምና እመቤታችን ዕፀ ጳጦስ ዘሲና ትባላለች::(110) ሊቀ ነቢያት ሙሴም በሲና ተራራ የተመለከተው ራእይ ረቂቅ ከመሆኑ የተነሣ "ልሂድና ቁጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ" (ዘጸ. 3÷3) በማለት አድንቋል:: የዚህ አማናዊ ምሳሌ ተስፋ ሲፈጸም አማናዊቷ ዕፀ ጳጦስ እመቤታችን አብሣሪዋን መልአክ "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆንልኛል?" (ሉቃ. 1÷34) ስትል በእርሷ ሕይወት ልዑል እግዚአብሔር የሚገልጠው የተዋሕዶ ምሥጢር ጥልቅና ረቂቅ መሆኑን መስክራለች::

ዳግመኛም ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት በአንቀጸ ብርሃን ደርሰቱ "አንቲ ኮንኪ ማኅደረ መለኮት፤ ወኢያውዐየኪ እሳተ መለኮት፤ ፃርኪ ነበልባለ እሳት ወኢያውዐየኪ ነበልባለ መለኮት፤ ተመሰልኪ ዕፀ ጳጦስ ዘርእየ ሙሴ በነደ እሳት ወዕፀታ ኢውዕየ፤ ከማሁ ኢያውዐየኪ እግዚእ ኃይላት ዘኮነንታሁ እሳት ፍጹም፤ አንቲ በአማን ዘኮንኪ ምክሐ ዘመድነ፤ አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ ለመለኮት ማደሪያ ሆንሽ:: እሳተ መለኮቱም አላቃጠለሽም:: ዳግመኛም የሚያቃጥለውን ነደ እሳት በማኅፀንሽ ተሸከምሽው፤ ነደ እሳትነቱ ግን ፈጽሞ አላቃጠለሽም:: ስለዚህም ሙሴ ሳትቃጠል በደብረ ሲና ባያት በዕፀ ጳጦስ ተመሰልሽ:: ሁለንተናው ፍጹም እሳት የሆነ የኃያላን ጌታ በማኅፀንሽ ባደረ ጊዜ የመለኮትነቱ እሳት አላቃጠለሽምና:: ዳግመኛም የባሕርያችን መመኪያ የሆንሽን አንቺ ነሽ"(111) ሲል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአምላክ እናትነት የበቃችበትን ልዩ ጸጋና ፍጹም ክብር አስረግጦ ተናግሮአል::

(110) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 118-119:: ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 386:: Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 98. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha], "*መጽሐፈ ምሥጢር*" [*"The Book of Mystery"*], ገጽ 8::

(111) ቅዱስ ያሬድ፣ "አንቀጸ ብርሃን"፣ ገጽ 412::

ይሁን እንጂ መልአክ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ከሰው ልጆች ኀሊናና ከቅዱሳን መላእክት አእምሮ በላይ የሆነው ይህ መለኮታዊ ምሥጢር የሚፈጸመውና የሚከናወነው ከሃሌ ኩሉ (ሁሉን ቻይ) በሆነው አምላክ ኃይልና ፈቃድ መሆኑን በመግለጥ "እስመ አልቦ ነገር ዘይስዓኖ ለእግዚአብሔር፤ ሁሉን ማድረግ የሚቻለውና ምንም ምን የሚሳነው ነገር የሌለ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር እመቤታችንን እንበለ ዘርእ፣ እንበለ ሩካቤ ፅንሳ እንድትወልደው ቢያደርግ የሚያግደውና የሚከለክለው አንዳችም ነገር አለመኖሩን በአጽንኦት መስክሮአል።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮም ከላይ የገለጥነውን ቃለ መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ቅድስት ድንግል እመቤታችን በአማን ወላዲተ አምላክ፣ በአማን ወላዲተ ቃል መሆኗን በግልጥ ያስተምራል። ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በዘወትር ምስጋናዋም "አንቲ ውእቱ ዕፀ ዘርእየ ሙሴ በነደ እሳት ወኢትውዒ፤ ሙሴ ነደ እሳት ሰፍሮባት፤ በነደ እሳት ተከባ ሳትቃጠል በደብረ ሲና ያያት ዕፅ አንቺ ነሽ። ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሔር መጽአ ወኀደረ ውስተ ከርሥኪ። ይኸውም ነደ እሳት የተባለው ወደዚህ ዓለም መጥቶ በማኅፀንሽ ያደረው የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅ ነው።"[112] እያለች ምልዕተ ጸጋ፣ ምልዕተ ክብር የሆነች እመቤታችንን የምታመሰግናት ስለዚህ ነው።

ከላይ በገለጥነው መሠረት ቅድስት ድንግል እመቤታችን "ወላዲተ አምላክ" የመሆኗ ምሥጢር አስቀድሞ የታወቀና የተረዳ እውነታ መሆኑን ይገነዘቧል። ከዚህም ጋር ልናስተውለው የሚገባን ዐቢይ የድኅነት ምሥጢር ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር እሥራኤል ዘሥጋን ከግብፅ ባርነት ነጻ ለማውጣት፤ እንዲሁም ከፈርዖን አገዛዝና ቀንበር ለማዳን በፈቀደና በወደደ ጊዜ በአምሳለ ነበልባል ወሐመልማል እንደተገለጠ ሁሉ፤ እሥራኤል ዘነፍስ የተባሉ ምእመናንን ከኃጢአት ቀንበር ነጻ አድርጎ ከሞት ቁራኝነትና ከሲኦል አገዛዝ ለማዳን አስቀድሞ የሰጠው የተስፋ ድኅነት ቀጠሮ በደረሰ ጊዜ ባሕርየ መለኮቱን ከአማናዊቷ ዕፀ

(112) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 50-51።*



ጳጦስ ከድንግል ማርያም ባሕርይ ጋር አዋሕዶ፤ በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ በመታየት ነው። በዚህም ረቂቅና ጥልቅ የሥጋዌ ምሥጢር ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሱታፌ በጉላ በተረዳ ምሥጢር መገንዘብ ይቻላል።

## 3.1.2 ልዑለ ቃል ኢሳይያስ ስለ አማኑኤል የተናገረው ቃለ ትንቢት

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ስለ ቅዱስ አማኑኤል አሰምቶ የተናገረው ቃለ ትንቢት በድንግል ማርያም መፈጸሙ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ፣ እመ አዶናይ መሆኗን ያስረዳል። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይህንን የኢሳይያስ ቃለ ትንቢት "ደረቅ ሐዲስ ኪዳን" ይሉታል። ይህም የሆነበት ምክንያት እንደሌሎቹ ቅዱሳን አበው ወይም ቅዱሳን ነቢያት በምሳሌ የተናገረው ሳይሆን በቀጥታ "እነሆ፥ ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች፣ በድንግልናም እግዚአብሔር ወልድን ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" (ኢሳ. 7፥14) በማለት የመድኅነ ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን ድንግልናዊ ልደት በግልጥ መስክሮአል።

በመሆኑም ይህ የድኅነተ ዓለም ተስፋ ትንቢት በዘመነ ሐዲስ በእመቤታችን መፈጸሙን አስመልክቶ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ሲናገር "በነቢይ ከጌታ ዘንድ፦ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች እግዚአብሔር ወልድን ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም፦ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው የሚል ነው።" (ማቴ. 1፥22-23) ሲል በአጽንኦት ገልጾአል። በዚህም ወንጌላዊው የወላዲተ አምላክ በግብረ መንፈስ ቅዱስ መፅነስና መውለድ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ከሥጋዌው አስቀድሞ በነቢዩ በኢሳይያስ አድሮ የተናገረው ቃለ ተስፋ ፍጻሜ መሆኑን አስረግጦ መስክሮአል።

በምሥጢረ ተዋሕዶ ትምህርት አማኑኤል የሚለው ስም የአካላዊ ቃል ብቻ ወይም የትስብእት ብቻ ስም አይደለም:: ይልቁንም አምላክ ሰው፤ ሰው አምላክ ሲሆን ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆኑ ሥግው ቃል የሚጠራበት፣ የሚመለክበትና የሚመሰገንበት የተዋሕዶ ስሙ ነው:: ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘአንጾኪያ "ስሙ ለምንታዌ ሰእተታ ተዋሕዶ፤ ምሥጢረ ተዋሕዶ ምንታዌን (ሁለትነትን) አስቀርቷል፣ አስወግዷል"[113] ብሎ እንዳስተማረው አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው:: ትርጓሜ ምሥጢሩም ወልደ እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋ፣ ከነፍሳችን ነፍስን ነሥቶ በተዋሕዶ ከእኛ ጋር አንድ አካል፣ አንድ ባሕርይ ሆነ ማለት ነው:: በዚህም ባሕርያዊ ተዋሕዶ የቃል ገንዘብ ለሥጋ፣ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ስለሆነ እመቤታችን ወላዲተ አምላክ፣ ወላዲተ ቃል ናት::

ከላይ ከገለጥነው በተጨማሪም ይህ የኢሳይያስ ቃለ ትንቢት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ሱታፌ በጉልህ ያሳያል:: ይኸውም ከእርሷ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በኅቱም ድንግልና የተወለደው አምላክ አማኑኤል (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ) መባሉ በኃጢአቱና በበደሉ ምክንያት ከእግዚአብሔር አንድነት ተለይቶ የነበረው የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር የታረቀባትና አንድ የሆነባት ሙሐዳተ ሕይወት፣ ምክንያተ ድኅነት መሆኗን ያረጋግጣል:: ስለዚህም መጽሐፍ "ሞታ ለነፍስ ርኂቅ እምእግዚአብሔር፤ የነፍስ ሞቷ ከእግዚአብሔር አንድነት መለየት ነው" እንዳለው ከአምላኩ አንድነት በመለየቱ ሞተ ነፍስ የሠለጠነበት የሰው ዘር ዳግመኛ በሐዲስ ተፈጥሮ በመታደሱና በመቀደሱ ምክንያት ሕይወትንና ድኅነትን ያገኘው፣ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውንም ኅብረት እንደገና የመሠረተው በድንግል ማርያም አማካይነት መሆኑን ልብ ይሏል::

[113] ቅዱስ ባስልዮስ ዘአንጾኪያ፣ "በእንተ ምሥጢረ ተዋሕዶ"፣ ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ 422::



ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ እግዚአብሔር ወልድ በእመቤታችን በኩል የገለጠው የድኅነት ምሥጢር እንዲሁም በእርሷ አማካይነት የፈጸመው አምላካዊ የቸርነትና የቤዛነት ሥራ እስከ ኅልቀተ ዓለም ድረስ ጸንቶ የሚኖር መሆኑን ተናግሮአል:: ይህም ይታወቅ ዘንድ ጸሐፊ ወንጌሉን "አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው" (ማቴ. 1፥23) በሚለው ቃለ ብሥራት ጀምሮ "እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ. 28÷20) ሲል አማኑኤል አምላካችን ለወዳጆቹ ለቅዱሳን ሐዋርያት የሰጣቸውን ቃለ ተስፋ በማውሳት መፈጸሙ በቂ ማስረጃችን ነው:: ይህንን ፍሬ ተዋሕዶ መሠረት በማድረግ ኢትዮጵያዊው የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "ተወልደ በተድባ መለኮት፤ ወልደ እግዚአብሔር ለመለኮት በሚገባ ልደት ተወለደ"[114] በማለት በአጽንኦት ገልጾአል::

ኢትዮጵያውያን መተርጉማንም የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ በማኅፀነ ድንግል የተከናወነው እንበለ ዘርዐ ብእሲ በመሆኑ በኅቱም ድንግልና የተፈጸመው የወልደ እግዚአብሔር ደኃራዊ ልደት ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት ለተወለደው ለአካላዊ ቃል የሚገባ ልደት ነው በማለት በምሥጢር ያራቅቁታል:: ዳግመኛም በማኅፀነ ድንግል ማርያም ያደረውና በኤፍራታ ቤተ ልሔም የተወለደው መድኅን ክርስቶስ አምላክ ካልሆነ ነቢዩ ኢሳይያስ ደፍሮ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች እግዚአብሔር ወልድንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች ሲል እንደምን ደፍሮ ተናገረ? ዳግመኛስ ወንጌላዊው የመልአኩን ቃል ጠቅሶ አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለቱ ስለምንድን ነው?[115] ስለሆነም ከላይ የገለጥነው የነቢዩ፣ የመልአኩና የወንጌላዊው ምስክርነት የሥጋዌውን አማናዊነትና የቅድስት ድንግል እመቤታችንን ወላዲተ አምላክነት በአጽንኦት ይመሰክራል፣ ያስገነዝባልም::

[114] ቅዱስ ያሬድ፣ ዝማሬ መዋሥዕት፣ ገጽ 55-56:: ቅዱስ ያሬድ፣ መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ- 225::

[115] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha], "መጽሐፈ ምሥጢር" ["The Book of Mystery"], ገጽ 9፣ 229:: Bauer, *The Essential Mary Handbook: A Summary of Beliefs, Devotions, and Prayers*, 26-27.

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክነት የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ድኅነት ትምህርት መሠረት ነው:: ምክንያቱም ከፈጣሬ ዓለማት ከእግዚአብሔር በቀር በኃጢአት የወደቀውንና በፍዳና በመርገም ተይዞ የነበረውን ዓለም ሊያድንና ወደ ቀደመ ክብሩ ሊመልስ የሚችል ሌላ አንዳችም ኃይል የለምና ነው:: ከዚህም ጋር የሰው ልጆች ድኅነት የሚገኘው ለራሱ ድኅነትን ከማይሻው አምላክ ዘንድ ብቻ መሆኑንም ልብ ይሏል:: በመሠረቱ ነገረ ድኅነት የትምህርተ ክርስትና ዐቢይ እውነታ ነው:: በመሆኑም የሰው ልጆች ድኅነት ፈጣሬ ፍጥረታት የሆነው ልዑል እግዚአብሔር በምሥጢረ ሥጋዌ አማካይነት ያደረገው ሐዲስ ተፈጥሮ በመሆኑ ይህን የአድኅኖት ሥራ ሊፈጽም የሚችለው ብቸኛው አካል በጥንተ ተፈጥሮ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ፤ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" (ዘፍ. 1፥26) ብሎ የሰውን ልጅ ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ይልቅ አልቆና አክብሮ በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው መፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር ብቻ ነው::

በዚህም ምሥጢረ ድኅነት መሠረት ከድንግል ማርያም የተወለደው መድኅን ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑን ይመሰክቷል:: ዳግመኛም ቅድስት ድንግል እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መባሏ የተገባና ከነገረ ድኅነት ምሥጢር ጋር የተስማማ እንደሆነ እንረዳለን፣ እንገነዘባለንም:: ከዚህም ጽንሰ ሐሳብ በመነሣት ከላይ የዘረዘርናቸውን ማስረጃዎች አብነት በማድረግ ወላዲተ አምላክ በነገረ ድኅነት ውስጥ ያላትን ጉልህ ድርሻ በግልጥ ማየትና ማስተዋል ይቻላል::[116]

ዳግመኛም በወንጌለ ቅዱስ ማቴዎስ እንደተጠቀሰው በኤፍራታ ቤተ ልሔም ከድንግል የተወለደው ሕፃን ስሙ ኢየሱስ ተብሎ እንደተ ጠራም ተገልጿል:: የስሙ ምሥጢራዊ ትርጓሜም ሕዝቡን

(116) Kelly, *Early Christian Doctrines*, 378. Tambasco, *What are they Saying about Mary?*, 40-41. Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 31.



በኃጢአትና በበደል ምክንያት ከመጣባቸው ፍዳና መርገም የሚያድን፣ በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን የሚያድል፣ ድኅነተ ሥጋና ድኅነተ ነፍስን የሚሰጥ አዳኝ የሆነ ጌታ ማለት ነው:: (ማቴ. 1፥21) ስለዚህም ከቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደው መድኅን ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ስለሆነ መድኃኒትነቱ እሙን ነው:: ከዚህም ሌላ የአዳኙ መገለጥ የሰው ልጆችን ለማዳን በመሆኑ ከወላዲተ አምላክ ከድንግል ማርያም የተገኘው ፍሬ ማኅፀኗ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ነው::

በመሆኑም ከላይ የገለጥነውና የተመለከትነው የድኅነተ ዓለም ምሥጢር ቅድስት ድንግል እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መሆኗን በግልጥ ይመሰክራል:: ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም ይህን ረቂቅና ጥልቅ ምሥጢር ሲያደንቅ "ለ ዝ መንክር ለደተ አምላክ እማርያም እምቅድስት ድንግል፤ ንዕድ ክብርት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስተ ቅዱሳን፣ ከንጽሕተ ንጹሐን፣ ከክብርተ ክቡራን፣ ከልዕልተ ልዑላን ከድንግል ማርያም ለሆነ ለዚህ ለአምላክ መወለድ አንክሮ ይገባል::"[117] በማለት ተናግሯል::

## 3.1.3 ነቢዩ ሚክያስ ስለ ኤፍራታ ቤተ ልሔም የመሰከረው ትንቢታዊ ቃለ ተስፋ

ነቢየ እግዚአብሔር ሚክያስ የተናገረው ይህ መሲሐዊ ቃለ ትንቢት የመድኅን ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መምጣትና በሥጋ ማርያም የመገለጡን ምሥጢር ያመለክታል:: የድኅነተ ዓለምን ዜና የሚያበሥረው ይህ ተስፋ ትንቢት ዕፁብ ድንቅ የሆነውን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሥጢረ ልደት ያስተረጉማል:: ስለሆነም ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር በነቢዩ ሚክያስ አድሮ የሥጋዌውን ነገር ሲያስረዳ "አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእሥራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል"

(117) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 128::

(ሚክ. 5÷2) በማለት ተናግሮአል:: ይህ የድኅነተ ዓለም ተስፋ ትንቢት ንጉሥ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በኤፍራታ ቤተ ልሔም በከብቶች ግርግም በተወለደ ጊዜ መፈጸሙንና መታተሙን ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ገልጾአል:: (ማቴ. 2÷1-11)

ከላይ የጠቀስነው ቃለ ትንቢት ትርጓሜ ምሥጢሩ የይሁዳ ዕፃ የሆነችው ቤተ ልሔም እሥራኤል ዘነፍስን በትምህርትና በተአምራት የሚጠብቃቸው ንጉሠ ሰማይ ወምድር ኢየሱስ ክርስቶስ የሚወለድባት በመሆኑ የይሁዳ ነገሥታት ከነገሡባቸው አህጉር የምትበልጥና የከበረች እንደምትሆን ያስረዳል፣ ያስገነዝባል:: በዚህም የንጉሥ ክርስቶስ ልደት ምክንያት ኤፍራታ ቤተ ልሔም የብርሃን ድንኳን ተተክሎባታል፣ መላእክትና ኖሎት (እረኞች) በአንድነት ዘምረውባታል፣ ሰብአ ሰገል ለአምላክነቱ፣ ለጌትነቱ የሚገባ እጅ መንሻን ገብረውባታል::

ዳግመኛም ይህ ተስፋ ትንቢት የኤፍራታ ልጅ የሆነችው አማናዊቷ ቤተ ልሔም ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም እሥራኤል ዘነፍስን በቃሉ ትምህርት፣ በእጁ ተአምራት የሚጠብቀውና በመንፈስ ልደት የሚያከብረው ሰማያዊው ንጉሥ ክርስቶስ ስለተገኘባት ጠበበተ ፍጡራን መሆኗንም ይመሰክራል::[118]

ኤፍራታ ቤተ ልሔም በቀድሞ ስሟ ከብታ ተብላ ትጠራ ነበር:: ከብታ ማለትም ቤተ ስብሐት (የምስጋና ቤት) ማለት ነው:: በምሥጢራዊ ትርጓሜውም ቤት የተባለችው አማናዊቷ ማኅደረ መለኮት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት:: ስብሐት የተባለው ደግሞ እግዚእ ስብሐት፣ እግዚእ ውዳሴ የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ከዚህም ሌላ ኤፍራታ ማለት ፀዋሪተ ፍሬ (ፍሬ የተሸከመች) ማለት ነው:: ጸዋሪት የእመቤታችን የድንግል ማርያም

[118] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 71-74:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha], *መጽሐፈ ምሥጢር* [*" The Book of Mystery"*], ገጽ 6፣ 17:: Meersseman, *The Acathistos Hymn: Hymn of Praise to the Mother of God*, 55.



ምሳሌ ሲሆን ፍሬ ደግሞ የማኅፀኗ ፍሬ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው::[119]

ይህንን አስመልክቶ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ሲናገር "... ፍሬ ከርሣ ለድኅነ ኵሉ ዓለመ:: ወሠዐረ እምኔነ መርገመ"[120] ብሏል:: ትርጓሜ ምሥጢሩም የማኅፀኗ ፍሬ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ሁሉ ከመከራ ሥጋ፣ ከመከራ ነፍስ፤ ከሞተ ሥጋ፣ ከሞተ ነፍስ አዳነ፤ በኃጢአትና በበደል ምክንያት የመጣብንን መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስን አጠፋልን፣ ደመሰሰልን ማለት ነው:: ቤተ ልሔም የሚለው ስያሜ ቤት፡- አደረ፤ እንዲሁም ለሔም፡- ኅብስት ከሚሉት ሁለት ሥርወ ቃላት የተገኘ ሲሆን ቤተ ልሔም ማለት ትርጓሜው ቤተ ኅብስት (የእንጀራ ቤት) ማለት ነው:: ይኸውም ቤት የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምሳሌ፣ ኅብስት ደግሞ የአማናዊው ኅብስተ ሕይወት የጌታ ምሳሌ ነው:: ራሱ ባለቤቱ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር "አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት፤ ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ::" (ዮሐ. 6÷51) እንዳለ::

ከላይ በገለጥነው ቃለ ትንቢት መሠረት ለጊዜው እሥራኤል ዘሥጋን የሚጠብቃቸው ንጉሥ ዘሩባቤል መነሣቱ ሕዝበ እሥራኤል ከባቢሎናውያን የባርነት ቀንበር ነጻ ለመውጣታቸው ምልክት እንደሆነ ሁሉ፤ እሥራኤል ዘነፍስን የሚጠብቀው ዘላለማዊው ንጉሥ ክርስቶስ በኤፍራታ ቤተ ልሔም መወለዱ ደግሞ እሥራኤል ዘነፍስ የተባሉ ምእመናን ከኃጢአትና ከሞት ቀንበር ነጻ ለመውጣታቸው ምልክት ነው:: ይህ የነቢዩ ሚክያስ ተስፋ ትንቢት በዘመነ ብሉይ ስለ ወላዲተ አምላክ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ከተነገሩት አያሌ ኀብረ ትንቢት መካከል አንዱና ዋነኛው መሆኑን በመግለጥ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ

[119] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 71:: ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 135-139:: ቅዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 107:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha], "መጽሐፈ ምሥጢር" ["The Book of Mystery"], ገጽ 95::

[120] ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 156::

ዘወትር የሚዘመረው የእመቤታችን ውዳሴ ከቅዱስ ዳዊት ቃለ ትንቢት ጋር በማገናዘብ በስፋት ያስረዳል::(121)

በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለጸው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ለወዳጁ ለቅዱስ ዳዊት ከባሕርዩ የሚከፈለውን ልጁን በዙፋኑ እንደሚያኖርለት በመሐላ አጽንቶለታል:: (2ኛ ሳሙ. 7÷12-14) ይህ አምላካዊ ተስፋም ለጊዜው የአብራኩ ክፋይ በሆነው በልጁ በሰሎሞን የተፈጸመለት ሲሆን፤ ፍጻሜ ምሥጢሩ ግን በኋለኛው ዘመን በሥጋዌ ርስት ወልደ ዳዊት መባልን ገንዘብ ባደረገው በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጽሟል::

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት በመጽሐፈ መንፈስ ቅዱስ የራቀው ምሥጢር ቀርቦለት፣ የረቀቀው ደግሞ ጐልቶለት ስለ ሥጋዌ ምሥጢር ሲናገር «ናሁ ሰማዕናሁ በኤፍራታ፤ ወረከብናሁ ውስተ ዖመ ገዳም»፤ እነሆ ወልደ እግዚአብሔርን በኤፍራታ ተወልዶ፤ በጎል ተጥሎ፤ በጨርቅ ተጠቅልሎ፤ በግዕዘ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው አለ:: ዳግመኛም «አንተ ኦቤተ ልሔም ዘኃፈያ አማኑኤል ይትወለድ ውስቴታ በሥጋ ለመድኃኒተ ዚአነ» በማለት ገጸ ንባቡን በትርጓሜ አጸናው፣ አጸደቀው፣ አተመው:: ትርጓሜ ምሥጢሩም የመድኅን ክርስቶስ መገለጫውና አማኑኤል አምላካችን እኛን ለማዳን በሥጋ ይወለድባት ዘንድ የመረጣትና ያከበራት ይህቺ ቤተ ልሔም ናት ማለት ነው:: ይኸው የእመቤታችን ውዳሴ ከዚህ በማያያዝ ሲናገር:- «ካዕበ ይቤላ ካልዕ እምነቢያት፤ ከነቢያት አንዱ ሚክያስ ዳግመኛ እንዲህ አላት...» ሲል ከላይ በዝርዝር የተመለከትነውንና ነቢዩ ሚክያስ ስለ ኤፍራታ ቤተ ልሔም የተናገረውን ቃለ ትንቢት አምልቶና አስፍቶ ይገልጻል:: በመቀጠልም ሁለቱ ነቢያት ከአንድ መንፈስ ቅዱስ አግኝተው የተናገሩትን ይህን ተስፋ ትንቢት በማድነቅ ሲጽፍ «ኦ ዝ ነገር ዕፁብ እለ ተነበዩ ዘበአሐዱ መንፈስ በእንተ ክርስቶስ፤ በአንድ መንፈስ ቅዱስ ተገልጾላቸው ነቢዩ ሚክያስና

(121) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 138::* Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia,* 166.



ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን ለተናገሩት ለዚህ ታላቅና ድንቅ ምሥጢር አንክሮ ይገባል»(122) በማለት ያስገነዝባል::

በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አስተምህሮ መሠረት ምሥጢረ ልደት ከምሥጢረ ስቅለት ጋር የተያያዘ ጥልቅና ረቂቅ ምሥጢር አለው:: ይኸውም በአጭሩ ሲገለጽ በዕለተ ልደት የተገለጠው አምላካዊ ምሥጢርና የተፈጸመው ድርጊት በአጠቃላይ መድኅነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በፈቃዱ ስለ እኛ የተቀበለውን መከራ መስቀልና የቤዛነት ሞት በምሥጢር ያሳያል:: ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ በዕለተ ልደት በኮከብ ተመርተው ወደ ኤፍራታ ቤተ ልሔም የመጡት ሰብአ ሰገል (የጥበብ ሰዎች) በከብቶች ግርግም በፍጹም ትሕትና ተኝቶ ለነበረው አምላክ ካቀረቡት አምኃ አንዱ ከርቤ ነበር::

የዚህ ገጸ በረከት ትርጓሜ ምሥጢርም ከርቤ መራራ እንደሆነ ሁሉ ቀዳማዊ ወደኃሬዊ የሆነው ጌታም በለበሰው ሥጋ መራራ የሞት ጽዋን የሚቀምስ (የሚቀበል) መሆኑን የሚያሳይ ነው:: ከዚህም ጋር ከርቤ የተሰበረውን የሚጠግን፣ የተለያየውን አንድ የሚያደርግ ነው:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሕማሙና በሞቱ በኃጢአትና በበደል ምክንያት ከእግዚአብሔር አንድነት የተለየውንና ከማኅበረ መላእክት የራቀውን አዳምን ከቁስለ ኃጢአቱና ከደዌ ነፍሱ ፈውሶ፤ ጽንዐ ነፍስን ሰጥቶ ወደ ቀደመ ክብሩ የሚመልሰው መሆኑን በምሥጢር ያስረዳል::(123)

ይህንን አስመልክቶም ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ሲናገር «... ሎቱ ሰገዱ ሰብአ ሰገል አምጽኡ ዕጣነ ከመ አምላክ ውእቱ፤ ወርቀ እስመ ንጉሥ ውእቱ፤ ወከርቤ ዘይትወሀብ ለሞቱ ማሕየዊ በእንቲአነ ተወከፈ በፈቃዱ፤» ሰብአ ሰገል ከመሬት ላይ ወድቀው፣ ተደፍተው ሰገዱለት:: የባሕርይ አምላክ

(122) *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 135-139::*

(123) *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 75:: ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 129-131::

መሆኑን ለማጠየቅ ዕጣን አመጡለት፤ በባሕርይው ሞት፣ ሽረት፤ በመንግሥቱም ኅልፈት፣ ውላጤ (መለወጥ) የሌለበት ሰማያዊና ዘላለማዊ ንጉሥ እንደሆነ ለማጠየቅ ወርቅ አመጡለት:: ዳግመኛም ሕይወትን የሚሰጥ ጌታ ስለ እኛ በፈቃዱ ወደ ለሚቀበለውና ማኅየዊ ለሚሆን ለሕማሙና ለሞቱ ምሳሌ ከርቤን አመጡለት አለ::[124]

ዳግመኛም የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን ከርቤን የፍቅር ምሳሌ አድርገው ወስደውታል:: ምክንያቱም ከርቤ የተለያየውን አንድ እንደሚያደርግ ሁሉ ጌታችንም የሰው ልጆች ፍቅር አገብሮት ባደረገው አምላካዊ የቸርነትና የማዳን ሥራው ሰውና እግዚአብሔርን፣ ሰውንና መላእክትን፣ ነፍስና ሥጋን፣ ሕዝብና አሕዛብን አስታርቆ አንድ አድርጓልና ነው:: ስለሆነም መጻሕፍት አምላካውያት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወሰን በሌለው ፍቅሩ ለሰው ልጆች የፈጸመውን የቤዛነት ሥራ በመተባበር ይመሰክራሉ:: ለዚህም "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና::" (ዮሐ. 3÷16)፤ "እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ::" (ዮሐ. 12÷32)፤ "ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም::" (ዮሐ. 15÷13) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎች ናቸው::

ሌላው ደግሞ ከላይ የገለጥነውን የነቢዩ ሚክያስ ቃል ተስፋ አስመልክቶ ነቢየ እግዚአብሔር ዕንባቆም "እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራህኩ:: ርኢኩ ግብረከ ወአንከርኩ:: በማዕከለ ክልኤ እንስሳ ርኢኩከ" በማለት የተናገረው ቃለ ትንቢት ነው:: ነቢዩ በሥጋዌ ርስት ተገብቶ የገለጠው ይህ ታላቅና ድንቅ ምሥጢር መድኅነ ዓለም ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የሠራውን አምላካዊ የትሕትና ሥራ የሚያስረዳና የሚያስገነዝብ ነው:: ትርጓሜ ምሥጢሩም አቤቱ ልዑለ ባሕርይ ጌታ

[124] ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 75-76:: ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 135-139::



እግዚአብሔር ሆይ ግሩም የሆነውን ድምፅህን ሰምቼ፤ አንድም በግዕዘ ሕፃናት ሆነህ ስታለቅስ ሰምቼ ፈራሁ፣ ደነገጥሁም:: ዳግመኛም የሰው ልጆች ፍቅር ቢያገብርህ በአጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስነህ፣ በሥጋ ማርያም ተገልጠህ የሠራኸውን አምላካዊ የቸርነት ሥራህን አይቼም በእጅጉ አደነቅሁ:: ስለዚህም በሁለት እንስሳት (በላሞችና በአህዮች) መካከል በፍጹም ትሕትና ሆነህ በግርግም ተኝተህ አየሁህ[125] ማለት ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ስለ ጌታችን ምሥጢረ ልደት የተነገረው ይህ የነቢዩ ቃለ ትንቢት ምሥጢረ ስቅለትንም ይመለከታል:: ትርጓሜ ምሥጢሩም በአጭሩ ሲገለጥ አቤቱ ቸርና ታጋሽ፣ መሐሪና ይቅር ባይ አምላክ ሆይ ግሩምና ድንቅ የሆነውን አስፈሪ ድምፅህን፤ አንድም በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ሆነህ ያሰማኸውን ሰባቱን አጽርሐ መስቀል ማለትም "አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?" (ማቴ. 27÷46)፤ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" (ሉቃ.23÷34)፤ "አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ" (ሉቃ. 23÷46)፤ "እነሆ ልጅሽ እነኋት እናትህ" (ዮሐ. 19÷26-27)፤ "ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" (ሉቃ. 23÷43)፤ "ተጠማሁ" (ዮሐ. 19÷28)፤ "ተፈጸመ" (ዮሐ. 19÷30) ማለትህን ሰምቼ እጅግ ፈራሁ፣ ደነገጥሁም::

ዳግመኛም ስለ ሰው ልጆች ፍቅር ስትል በቅንዋተ መስቀል ተቸንክረህ፣ አክሊለ ሶክን ተቀዳጅተህ፣ መራራ ሐሞትን ጠጥተህ በቀራንዮ መስቀል ላይ ተሰቅለህ፣ ኅብስተ ሕይወት ቅዱስ ሥጋህን ቆርሰህ፣ ማየ ሕይወት ደምህን አፍስሰህ፣ ቅድስት ነፍስህን ክሰህ የፈጸምከውን የቤዛነት ሥራ አይቼ ፈጽሞ አደነቅሁ:: ስለዚህም በሁለት እንስሳት መካከል ማለትም በተፈጥሮአቸው ሰብአዊ ሆነው በግብራቸው ግን እንስሳትን በመሰሉት በሁለቱ ወንበዴዎች:- በፀጋማዊ ዘየማን (በጥጦስ) እንዲሁም በፀጋማዊ ዘጸጋም (በዳክርስ) መካከል ተሰቅለህ አየሁህ ማለት

[125] ትርጓሜ ዕንባቆም ነቢይ፣ (በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከመጋቤ ብሉይ መዘምር ታዬ የመጻሕፍተ ብሉያትን ትርጓሜ ከተማርኩበት ማስታወሻ የተሰወደ)::

ነው::[126] (ኢሳ. 53÷12፤ መዝ. 48÷12፤ ማቴ. 27÷38፤ ማር. 15÷27-28፤ ሉቃ. 23÷32-33፤ ዮሐ. 19÷18)

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ድንቅ በሚያሰኘው የተዋሕዶ ምሥጢር የተፈጸመውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ድንግልናዊ ልደት በተናገረበት አንቀጽ "ወወለደት ወልደ ዘበኩራ:: ወአሠረቶ ወኀኮብያቲሁ:: ወአስከበቶ ውስተ ጎል ወጠብለለቶ በአጽርቅት:: እስመ አልቦሙ መካን ውስተ ማኅደርሙ" (ሉቃ. 2÷7) ብሏል:: ምሥጢራዊ ትርጓሜውም ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም የበኩር ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን በወለደችው ጊዜ ዮሴፍ ዘአርማትያስና ኒቆዲሞስ በዕለተ ዓርብ እንዲህ አድርገው ይገንዙሃል ስትል አውራ ጣቱን አሰረችው ማለት ነው:: ከዚህም ጋር ለማደሪያቸው ቦታ አልነበራቸውምና አድግና ላህም አምኃ እስትንፋሳቸውን በሚገብሩለት ገንዘብ ያገለግሉትና ያከብሩት ዘንድ፤ ጌትነቱንም ይገልጡ ዘንድ ድንግል ልጇን በበረት አስተኛችው:: ዳግመኛም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በዕለተ ዓርብ በድርብ በፍታ እንዲህ አድርገው ይገንዙሃል ስትል በጨርቅ ጠቀለለችው ማለት ነው::[127]

ሶርያዊው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም መሲሕ ክርስቶስ በኤፍራታ ቤተ ልሔም በከብቶች ግርግም በፍጹም ትሕትና የመወለዱ ምሥጢር ዋና ዓላማ የተዋረደውንና በተናቀ ሥፍራ የወደቀውን የሰውን ሕይወት ለማክበር መሆኑን ገልጾአል:: ይህንንም ሲያስረዳ "... በመንጸፈ ደይን ሆነው ሲያዝኑና ሲተክዙ፣ የተሰጣቸውን ጸጋና ክብርም ትተውና ጥለው በምትኩ ቅጠልን የለበሱ አዳምና ሔዋን ወደ ቀደመው ሥፍራቸው ወደ ገነት ይመለሱ ዘንድ እነሆ አንተ ስለ እነርሱ ስትል በጨርቅ ተጠቀለልክ"[128] በማለት አምላካዊ ቸርነቱንና ፍጹም ትሕትናውን ያደንቃል:: (ዘፍ. 3÷7፤ ሉቃ. 2÷7)

---

(126) *ትርጓሜ ዕንባቆም ነቢይ*፣ (በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከመጋቤ ብሉይ መዘምር ታዬ የመጻሕፍተ ብሉያትን ትርጓሜ ከተማርኩበት ማስታወሻ የተሰወደ)::

(127) *ወንጌል ንቅዱስ ባቡና ትርጓሜው*፣ ገጽ 336::

(128) Brock, *Bride of Light*, 73. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት*፣ ገጽ 213-214::





ሥዕል 4:- ሰብአ ሰገል ለጌታ ሰግደው እጅ መንሻን እንደገበሩለት

"በጎለ እንስሳ ተወድዮ:: ለምኅ ንግሡ ተወፊዮ:: ወከመ ሕፃናት በከዮ እንዘ ይስእል እምአጥባተ እሙ ሲላዮ፤ በእንስሳት በረት ተጨመረ:: የንግሡንም እጅ መንሻ ተቀበለ:: ከእናቱ ጡቶች ምግብን እየለመነ እንደ ሕፃናት አለቀሰ::"

(መጽሐፈ ቅዳሴ፣ ገጽ 410)

## 3.1.4. ነቢዩ ዳንኤል በአምሳለ ዕብን ዘመልዕልተ ደብር ያየው ራእይ

ከዐበይት ነቢያት መካከል አንዱ የሆነው ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል ስለ እመቤታችን ወላዲተ አምላክነት በአምሳለ ደብር ነዋኅ (በ ረጅም ተራራ አምሳል) አይቷል:: ነቢዩ ይህ ረጅም ተራራ ታላቁን ምስል የቀጠቀጠውና ትቢያ ያደረገው ዕብን (ድንጋይ) የተገኘበት መሆኑን ተናግሮአል:: ዳግመኛም የሰው እጅ ሳይነካውና ሳይፈነቅለው ከተራራ ላይ የወረደው ይህ ድንጋይ ምስሉን እንደሰባበረውና እንዳደቀቀው፤ ከዚያም በኋላ ትቢያ የሆነውን ምስል ጽኑዕ የሆነ ነፋስ መጥቶ እንደበተነው፤ ድንጋዩም ተመልሶ ታላቅ ተራራ እንደሆነና ምድርን እንደመላም ነቢዩ አውስቷል:: (ዳን. 2÷31-35)

ይህንን አስመልክቶም ሊቁ ቅዱስ አባ ሕርያቆስ እመቤታችንን ባመሰገነበት ቅዳሴው "ብከ፡ርና እንበለ ሩካቤ ዘዳንኤል" ድንግል ሆይ ነቢዩ ዳንኤል "እብነ ዘተበትከ እምደብር ነዋኅ ዘእንበለ እድ፤ እጅ ሳይፈነቅለው ከ ረጅም ተራራ የወረደ ድንጋይ"[129] ብሎ በእደ ብእሲ መዳሰስ ሳይኖርብሽ አካላዊ ቃልን ያለ ዘር፣ ያለ ሩካቤ መውለድሽን የተናገረልሽ አንቺ ነሽ በማለት አመሰግኗታል:: ስለሆነም ይህ ታላቅ ድንጋይ የሰው እጅ ሳይነካው ከረጅም ተራራ ላይ መውረዱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከልዕልና ወደ ትሕትና ለመውረዱና እንበለ ዘርአ ብእሲ ከድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ለመወለዱ ምሳሌ ነው:: ይህም ትንቢታዊ ራእይ ዕብነ ሕይወት (የሕይወት ድንጋይ) የተባለ ጌታን በድንግልና ፀንሳ፣ በድንግልና የወለደች ቅድስት ድንግል እመቤታችን ወላዲተ አምላክ መሆኗን በግልጥ ይመሰክራል፣ ያረጋግጣልም::

ከላይ የገለጥነው ትንቢታዊ ራእይ ከነገረ ድኅነት ጋር ያለውን ጥልቅ ምሥጢር አስመልክቶ ቅዱስ ኤፍሬም ሲያስተምር:- "ነቢዩ

[129] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 104-1052:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ *መጽሐፈ ሰዓታት፣* ገጽ 156::



ዳንኤል እጅ ሳይፈነቅለው ከረጅም ተራራ ሲወርድ ያየው ድንጋይ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ዘንድ በትሕትና ወደዚህ ዓለም የመጣውና ዘር፣ ሩካቤ ምክንያት ሳይሆነው ከድንግል ተወልዶ ያዳነን አካላዊ ቃል ነው።"[130] ብሏል:: ከዚህም ኃይለ ቃል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ሰው የሆነበት የምሥጢረ ሥጋዌ ዋና ዓላማ የሰው ልጆች ድኅነት መሆኑን ይገነዘቧል:: ስለሆነም ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል ባየው በዚህ ታላቅና ድንቅ ራእይ እደ ብእሲ ሳይነካው ከረጅም ተራራ የወረደው ድንጋይ ምስሉን ካደቀቀው በኋላ ተመልሶ ትልቅ ተራራ እንደሆነ ተመልክተናል:: ይህም አማናዊ ምሳሌ በመዳን ትምህርት [Soteriology] መሠረት ሥጋ በተዋሕዶተ ቃል አምላክ መሆኑን ያጠይቃል:: ከዚህ በተጨማሪም ከተራራ የወረደው ድንጋይ ያደቀቀውን ምስል የበተነው ጽኑዕ ነፋስም ሥጋ በተዋሕዶ ገንዘብ ያደረገውን ሥልጣነ መለኮት ያመለክታል::

በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የነገረ ማርያም አስተምህሮ መሠረት በኃጢአት የወደቀው፣ በበደል የጎሰቆለውና ያደፈው የሰው ልጅ ንጽሐ ጠባይዕና ቅድስና ባሕርይ ዳግመኛ የከበረውና ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ ለመሆን የበቃው ወልደ እግዚአብሔር በማኅፀነ ድንግል ማርያም በተፀነሰበት ቅጽበት ነው:: ይህም ሊሆን የቻለው "እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ፣ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል፤ የቃል ገንዘብ ለሥጋ፣ የሥጋ ገንዘብ ለቃል ሆነ" በሚለው የምሥጢረ ተዋሕዶ ዐቢይ መርሕ ማለትም የሥነ መለኮት ሊቃውንት ኮሚዩኒኬሽዮ ኢድዮማተም *[Communicatio Idiomatum]* በሚሉት ዐቢይ የሥጋዌ መርሕ መሠረት ነው::

በዚህ ረቂቅና ድንቅ የሥጋዌ ምሥጢር ምክንያት ማኅፀነ ድንግል ማርያም መለኮትና ትስብእት የተገናኙባት፣ የተስማሙባትና የተዋሐዱባት የቅድስና አዳራሽ መሆኗን ይገነዘቧል:: ልበ አምላክ

[130] *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣* ገጽ 66-72:: Malaty (Fr.), *St. Mary in the Orthodox Concept*, 46.

የተባለው ቅዱስ ዳዊትም ይህንን ምሥጢር ሲገልጥ:- «ሣህል ወርትዕ ተ ራከባ:: ጽድቅ ወሰላም ተሰዓማ:: ርዕትሰ እምድር ሠረፀት፤ ይህም ማለት መለኮትና ትስብእት በማኅፀነ ማርያም ተገናኙ:: ትስብእት ከእመቤ ታችን ባሕርይ ተከፈለ፤ አካላዊ ቃልም ከአብ ተገኘ:: እመቤታችንም ሥጋዋን ነፍሷን በቅድስና በንጽሕና አጽንታ ለተዋሕዶ በቅታ ተገኘ ች»[131] ማለት ነው:: (መዝ. 84÷10-11)

ከላይ በገለጥነው ኦርቶዶክሳዊ የነገረ ማርያም ትምህርት መሠ ረት ነቢዩ ዳንኤል ዕብነ ሕይወት የተባለ ጌታን ያስገኘች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአማን ወላዲተ አምላክ፣ በአማን ወላዲተ ቃል የመሆኗን ምሥጢር በአምሳለ ደብር ነዋኅ (በረጅም ተራራ አምሳል) እንደመሰከረ ተመልክተናል:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ይህንን ትንቢታዊ ራእይ አራቅቀውና አመስጥረው ባስተማሩበት የምሥጢረ ሥጋዌ መድበላቸው:-

> ወለድኪ ተወልደ እምኔሃ ዘእንበለ ዘርአ ብእሲ በከመ ተብህለ በዳንኤል ነቢይ እምደብር ወረደ ዕብን ዘእንበለ እድ ወሐረጾ ለምስል፤ ወኮነ ውእቱ ምስለ ከመ ፀበለ ዐውድ:: ወዝኩሰ ዕብን ዘቀጥቀጦ ኮነ ደብረ ዐቢየ ወመልአ ኵሎ ምድረ:: ደብርሰ ይእቲኬ ማርያም ዘተወልደ እምኔሃ ዕብነ ሕይወት ዘእንበለ ይግስሳ እደ ብእሲ በሐውዘ ፍትወት ሥጋ::[132]

በማለት ተናግረዋል::

የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢሩም በነቢዩ በዳንኤል እንደተነገረው ከተራራ ላይ የሰው እጅ ሳይነካው ድንጋይ ወረደ፤ ምስሉንም ፈጨው፤ ምስሉም እንደ ሜዳ ትቢያ (አፈር) ሆነ:: ምስሉን የቀጠቀጠው ይህም ድንጋይ እነሆ ታላቅ ተራራ ሆነ፣ ምድርንም መላ:: ይህቺ ተራራም በሥጋ ፈቃድ ምክንያት የሚዘረጋ የሰው እጅ

[131] መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 426-427:: ድርሳነ ገብርኤል፣ ገጽ 19:: Davis, *The Seven Ecumenical Councils (325-787): Their History and Theology*, 327.

[132] Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 42. ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 66-72:: አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ [Abba Giyorgis of Gascha], "መጽሐፈ ምሥጢር" ["The Book of Mystery"], ገጽ 134-135::



ሳይነካትና ሳይዳስሳት ዕብነ ሕይወት (የሕይወት ድንጋይ) የሚሆን ጌታ ከእርሷ የተወለደ እመቤታችን ማርያም ናት:: ዳግመኛም ይኸው ሊቅ በሰዓታት ድርሰቱ "ዕብነ ሕይወት ወርእሰ ማዕዝንት ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ የሕይወት ድንጋይ፣ የማዕዘን ራስ የሆነው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»[133] ሲል አስረግጦ መስክሮአል::

እስትንፋሰ እግዚአብሔር የሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ዕብነ ሕይወት የተባለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ በተነገ ረለት ትንቢትና በተመሰለለት ምሳሌ መሠረት በኋለኛው ዘመን በሥጋ ማርያም መገለጡን በመተባበር ይመሰክራሉ:: ለዚህም «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፤ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ... በዚህም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፤ ድንጋዩ ግን የሚወድቅ በትን ሁሉ ይፈጨዋል» (ማቴ. 21÷42-44)፤ «እናንተ ግንበኞች የናቃች ሁት÷ የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው» (የሐዋ. ሥራ 4÷11) «ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈ ሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ::» (1ኛ ቆሮ.10÷3-4)፤ «እነሆ÷ የተመረጠና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ:: በእርሱም የሚያምን አያፍርም... እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፤ ለማያምኑ ግን አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ የማሰናከያም ዓለት ሆነ» (1ኛ ጴጥ. 2÷6-8፤ ኢሳ. 28÷16፤ መዝ. 117÷22፤ ኢሳ. 8÷14) የሚሉት ቃላተ መጻሕፍት በቂ ማስረጃዎችና ምስክሮችም ናቸው::

ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊስ «ዳንኤልኒ ነቢይ ... ዘተሰምዮ ብለማሶር ርእዮ ለማርያም በአምሳለ ደብር ወለወልዳኒ በአምሳለ ዕብን እስመ ይቤ ርኢኩ ተመትረ ዕብን እምደብር ዘእንበለ እድ:: ደብርሰ ይእቲኬ ማርያም ዘተወልደ እምኔሃ ወመድኃኔዓለም ዕብነ ሕይወት ወዕብነ መድኃኒት ለእለ የአምኑ ቦቱ»[134] ሲል

[133] አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ መጽሐፈ ሰዓታት፣ ገጽ 156::

[134] Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 100.

በዘመነ ብሉይ የተገለጠውን የነቢዩን ምሳሌ በዘመነ ሐዲስ ከተፈጸመው አማናዊ የድኅነት ምሥጢር ጋር በማገናዘብ አብራርቶና አፍታቶ ተናግሮታል። የኃይለ ቃሉ ፍቺም ብልጣሶር የተባለው ነቢዩ ዳንኤል ድንግል ማርያምን በተራራ አምሳል አያት፤ ልጇንም በድንጋይ አምሳል አየ። ከተራራ ላይ እጅ ሳይፈነቅለው ድንጋይ ሲወርድ አየሁ ብሏልና። ተራራ የተሰኘችውም በእርሱ ለሚያምኑበት ሁሉ የሕይወት ድንጋይ፣ የድኅነት ድንጋይ የሆነው መድኃኔዓለም ክርስቶስ ከእርሷ የተወለደ እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት ማለት ነው።

ከላይ የጠቀስናቸው ቃላተ መጻሕፍት ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያም ከሦስቱ አካላት አንዱን አካል እግዚአብሔር ወልድን መውለዷን በመግለጥ በአማን ወላዲተ አምላክ፣ በአማን እሙ አምላክ መሆኗን ይመሰክራሉ፣ ያረጋግጣሉ። በዚህም ድኅረ ዓለም ከእመቤታችን ያለ አባት በተወለደው ምድራዊ ልደት ወልደ ማርያም መባልን ገንዘብ ያደረገው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደው አካላዊ ቃል መሆኑን ልብ ይሏል። ከዚህ የወጣ ትምህርት ግን መሠረታዊውን የነገረ ድኅነት አስተምህሮን ይቃረናል፣ ያፋልሰዋልም።

ይኸውም ወልደ ማርያም (የድንግል ማርያም ልጅ) ወልደ አብ (የእግዚአብሔር አብ ልጅ) ካልሆነ ሕማሙና ስቅለቱ፣ ሞቱና ትንሣኤው ለድኅነታችን አንዳችም ረብ (ጥቅም) የለውም ማለት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የክርስትና እምነታችንንና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ብሎም ሰማያዊ ተስፋችንን ሁሉ ከንቱ ያደርገዋል።

ይህንን አስመልክቶ በዜና አበው ሊቃውንት ዘንድ "የመንፈስ ቅዱስ ዕንዚራ፣ የመንፈስ ቅዱስ በገና" በመባል የሚታወቀው ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያምን ባመሰገነበት ውዳሴው ሲናገር "አክሊሉ ዘእምቅድስት ሥላሴ ርእዮ ትሕትናነ አጽንዐ ሰማየ ሰማያት፤ ወወፅአ ወኃደረ ውስተ ከርሥ ድንግል፤ ወኮነ ሰብአ ከማነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ፤



ወተወልደ በቤተ ልሔም በከመ ሰበኩ ነቢያት አድኃነነ ወቤዘወነ ወፈሰየነ ሕዝበ ዚአሁ»(135) ብሏል።

የዚህ ገጸ ንባብ ምሥጢርም ልዩ ሦስት ከሚሆኑ ከአብ፣ ከወልድ፣ ከመንፈስ ቅዱስ አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በመንጸፈ ደይን መውደቃችንን፣ በእግረ አጋንንት መጠቅጠቃችንን፣ በፍዳና በመርገም መያዛችንን አይቶ ልዑል ባሕርዩን በትሕትና ዝቅ አድርጎ ወደዚህ ዓለም መጣ። ሰው ሆኖም በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ። ኩነቻዋ ከኃጢአት በቀር እንደ እኛ ፈጽሞ ሰው ሆነ። ከነቢያት መካከል እነ ሚክያስ "አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፣ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእስራኤልም ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል።" (ሚክ. 5፥2)፤ አንድም እነ ቅዱስ ዳዊት "እነሆ በኤፍራታ ሰማነው፤ በዱር ውስጥም አገኘነው።" (መዝ. 131፥6) ብለው እንደተናገሩ በቤተ ልሔም ተወለደ። ከኃጢአትና ከፍዳም ማኅየዊ በሚሆን ሞቱ አዳነን፣ ከእርግማን ሞትም በወርቀ ደሙ ዋጀን። ወደ እርሱም በሃይማኖት ተቀበለን፣ በመንፈስ ልደትም አከበረን፤ ወገኖቹም አደረገን ማለት ነው። (ሆሴዕ 2፥25፤ ሮሜ 9፥25-29፤ 1ኛ ጴጥ. 2፥9-10)

ዳግመኛም "አጽንነ ሰማየ ሰማያት ወወረደ ወኃደረ ውስተ ከርሠ ድንግል" የሚለው ኃይለ ቃል የሥጋዌን ምሥጢር አማናዊነት በግልጥ ያሳያል። ይኸውም አካላዊ ቃል እግዚአብሔር ወልድ የድኅነተ ዓለምን ሥራ በፈጸመበት የሥጋዌ ርስት የሰማያውያን መላእክትን ባሕርይ ባሕርዩ አለማድረጉን ያስገነዝበናል። ይልቁንም ምድራውያን የሚሆኑ የደቂቀ አዳምን ባሕርይ በተዋሕዶ ባሕርዩ አድርጎ በድንግል ማኅፀን እንዳደረ ያስረዳል።(136) ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም በመልእክቱ "እስመ አኮ እመላእክት ዘነሥአ ስዘነሥአ ዘእንበለ ዳዕሙ እምዘርዐ አብርሃም፤

(135) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 144-145።
(136) ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 144። ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 71-74።

የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም» (ዕብ. 2÷16) ሲል በአጽንኦት መስክሮአል:: የዚህም ኃይለ ቃል ትርጓሜ ምሥጢሩ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔር ከአብርሃም ዘር ወይም ባሕርይ የተገኘች የቤዛዊተ ዓለም ድንግል ማርያምን ሥጋን ተዋሐደ እንጂ የመላእክትን ባሕርይ አልተዋሐደም ማለት ነው:: (ማቴ. 1÷1)

መምህረ ቅዱሳን የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ ሲያስተምር "የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቶአልና:: ... ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን?" (ማቴ. 18÷11-12) በማለት መፍቀሬ ሰብእ የሆነ ቸር አምላክ መሆኑን በገለጠበትና ብዝኀ ርኅራኄውንም ባሳየበት በዚህ ምሳሌያዊ ትምህርቱ አስገንዝቦናል:: የዚህ ምሳሌ ትርጓሜ ምሥጢርም በአጭሩ ሲገለጥ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አንድ በግ የተባለ አዳም በኃጢአቱና በበደሉ ምክንያት ከፈጣሪው አንድነት፣ ከዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ኅብረት ተለይቶ በጠፋ ጊዜ፤ በዘጠና ዘጠኝ በጎች የተመሰሉ ቅዱሳን መላእክትን በከተማቸው በሰማይ ትቶ ማለትም ባሕርየ መላእክትን ባሕርዩ ሳያደርግ ከልዕልና ወደ ትሕትና ወርዶ ባሕርየ ሰብእን (የሰውን ባሕርይ) ባሕርዩ አደረገ ማለት ነው::[137] ይህ አምላካዊ ትሕትናም ቀደም ብለን በነቢዩ ዳንኤል ትንቢታዊ ራእይ ትርጓሜአችን ከተ መለከትነውና የድንጋዩ ከረጅም ተራራ መውረድ እግዚአብሔር ወልድ ከልዕልና ወደ ትሕትና መምጣቱን በምሥጢር ያመለክታል ካልነው ጋር የተገናዘበና የተሰናሰለም ነው::

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ መጽሐፍ "ስእምሩ ከመ ኅብረ ብሉይ ወሐዲስ በእንተ ማርያም ወበእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ርእዩ ከመ ይነግር ቀዳማዊ በእንተ ደኃራዊ ወደኃራዊ ይፌጽሞ፤ ብሉይና ሐዲስ ስለ ድንግል ማርያምና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድነት በመተባበር እንደተናገሩና እንደመሰከሩ

(137) *ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ* 183-184:: *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው፣ ገጽ* 418::



እወቁ፤ ዳግመኛም ብሉይ ኪዳን ስለ አዲስ ኪዳን እንደሚናገር አዲስ ኪዳንም ብሉይ ኪዳንን እንዲተረጉመው፣ እንዲፈጽመው፣ እንዲያጸናው እዩ፣ ተመልከቱም»[138] እንዳለ በምዕራፉ ውስጥ ያየናቸው የብሉይ ኪዳን ኅብረ አምሳልና ኅብረ ትንቢት በአዲስ ኪዳን በወላዲተ አምላክ በቅድስት ድንግል ማርያም መፈጸማቸውንና መታተማቸውን እንመለከታለን::

## 3.1.5 የብሉይና የሐዲስ ምሥጢራዊ ስምምነት

በዘመነ ሐዲስ በእግዚአብሔር ወልድ ሰው የመሆን ምሥጢር (በምሥጢረ ሥጋዌ) አማካይነት የተከናወነው የድኅነተ ዓለም ጉዞ እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ እንዲያው በድንገት ወይም በቅጽበት የተደረገ አይደለም:: ይልቁንም መፍቀሬ ሰብእ የሆነው ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር አስቀድሞ ወዶና ፈቅዶ ባናገረው ተስፋ ትንቢትና ባስመሰለው ምሳሌ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ልናስተውል ይገባል:: (ዕብ. 1÷1-2) ስለሆነም ለዚህ አምላካዊ የማዳን ሥራ ልዩ መሣሪያ እንድትሆን የተመረጠችውና የተዘጋጀችው ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም በመሆኗ የነገረ ድኅነት መሠረት ናት::

በኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት ዘንድ ታላቅና ልዩ የሆነ ሥፍራ ከሚሰጣቸው የክርስትና ምሥጢራት አንዱ ብሥራተ መልአክ ነው:: በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ መሠረት የመልአከ ሰላም የቅዱስ ገብርኤል ዜና ብሥራት የምሥጢረ ሥጋዌ መሠረት የተጣለበትና በማኅፀነ ድንግል ማርያም የድኅነተ ዓለም ሥራ የተጀመረበት ዐቢይ ምሥጢር ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ወደፊት በምዕራፍ አምስት በስፋት እንደምናየው ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት በወንጌለ ቅዱስ ሉቃስ መጀመሪያ ላይ የተገለጸውን የመጋቤ ሐዲስ የቅዱስ ገብርኤልን ዜና ብሥራት [Annunciation] (ሉቃ. 1÷26-38)፤

(138) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia*, 100-102.

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ቅድስት ኤልሳቤጥን የጎበኘችበትን [Visitation] (ሉቃ. 1÷39-45)፤ እንዲሁም የእመቤታችንን የምስጋና ጸሎት [*Magnificat*] (ሉቃ. 1÷46-53) አጠቃሎ የያዘውን ገጸ ንባብ **«የወንጌል ውዳሴ ማርያም»** ይሉታል::[139]

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ብሥራተ መልአክን ሲጽፍ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በስድስተኛው ወር የገሊላ ከተማ ወደ ሆነችው ወደ ናዝሬት ተልኮ ለእመቤታችን ለድንግል ማርያም መድኅን የሆነው አምላክ ከእርሷ በተዋሕዶ ሰው የመሆኑን ምሥጢር እንዳበሠራት ተናግሮአል:: በዚህም ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የድኅነተ ዓለምን የምሥራች ከሁሉ በፊት የሰማችና ያወቀች የእግዚአብሔር የምሥጢር መዝገብ፣ የምሥጢር ሙዳይ ናት:: ይህንን አስመልክቶ መጽሐፍ ሲናገር «ማርያም ይእቲ ዘቀደመት ተበስሮ ዜና ሥናየ ዘኢየኀልፍ እምኀበ ዝንቱ ክቡር መልአክ ገብርኤል»[140] ይላል:: ትርጓሜውም «ክቡርና ኃያል ገናና ከሆነው መልአክ ከቅዱስ ገብርኤል አንደበት የማይመረመረውንና ደስ የሚያሰኘውን የምሥራች ዜናን ከሁሉ ቀድማ የሰማችና የተበሠረችው ድንግል ማርያም ናት» ማለት ነው::

የቤተ ክርስቲያን መተርጉማን ብሥራተ መልአክ በስድስተኛው ወር የሆነበትን ምሥጢር ሲያብራሩ በዘመነ ብሉይ ከተፈጸመው ከሠለስቱ ደቂቅ (ሦስቱ ወጣቶች) ማለትም ከአናንያ፣ አዛርያና ሚሳኤል የድኅነት ታሪክ ጋር በማገናዘብ በጥልቀት አስተምረዋል:: እነዚህ ወጣቶች በዘመናቸው የነበረው ንጉሡ ናቡከደነፆር በሐቅለ ዱራ (በዱራ ሜዳ) ላይ ላቆመው የወርቅ ምስል ወይም ጣኦት እንዲሰግዱ በተጠየቁ ጊዜ «እምነ ንጉሥ ይኄይስ ለብነ፤ የአማንያን ልቡና ከንጉሥ ይልቅ ያዛልና» በጽንዐ ሃይማኖት ቆመው ለንጉሡ «የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል÷

(139) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia,* 15. ቅዱስ ያሬድ፣ *መጽሐፈ ድጓ*፣ ገጽ 171::

(140) Getachew Haile (Professor), *The Mariology of Emperor Zara Yacob of Ethiopia,* 44.



ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን÷ ንጉሥ ሆይ÷ እርሱ ባያድነን÷ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ» (ዳን. 3÷17-18) በማለት መለሱለት::

ናቡከደነፆርም በዚህ ምክንያት ተቆጥቶ ሠለስቱ ደቂቅ እጅ እግራቸውን ታስረው ወደ ሚነድደው እቶነ እሳት እንዲጣሉ አዘዘ:: በዚህም መሠረት ከንጉሡ ሠራዊት ውስጥ የተመረጡት ኃያላን እነዚህን ወጣቶች ወደ እሳቱ እቶን ጣሏቸው:: በዚህ ቅጽበት «ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ዘስሙ ገብርኤል፤ ወቀርበ ወዘበጦ ለነበልባለ እሳት በበትረ ብርሃኑ» እንዲል ሰማያዊው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ሰማያትን አቋርጦ፣ ደመናትን ሰንጥቆ ሠለስቱ ደቂቅ ወደ ተወረወሩበት እቶነ እሳት ውስጥ ወረደ:: እሳቱንም በያዘው በትረ መስቀል በመታው ጊዜ «ወኮነ ከመ ነፋስ ቈሪር» ይላል እሳቱ እንዳደረ ውርጭ ቀዝቃዛ ሆነ:: ሠለስቱ ደቂቅም ከእስራታቸው ተፈትተው፣ እሳቱ ሳያቃጥላቸውና አንዳችም ሳይጎዳቸው ከመልአኩ ጋር በደስታ እየዘመሩ በእሳቱ ጉድጓድ ውስጥ ተመላለሱ:: (ዳን. 3÷19-30፤ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅን ይመልከቱ)

ሠለስቱ ደቂቅ ልዑለ ባሕርይ እግዚአብሔር ተራዳኢና ታዳጊ የሆነውን መልአኩን ልኮ ከሚነድደው እሳት ስላዳናቸውና ከጽኑ እስራታቸውም ስለፈታቸው ልቡናቸው በደስታ ተሞልቶ እግዚአ ስብሐት፣ እግዚአ ውዳሴ (የምስጋናና የክብር ባለቤት) የሆነውን አምላክ በእሳቱ ጉድጓድ መካከል ሆነው፣ በስድስት አንቀጽ ወስነው፣ ስድስት ጊዜ መላልሰው ፈጽመው አመስግነዋል:: እነዚህ ወጣቶች እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው ቅዱስ እግዚአብሔርን ፈጽመው ያመሰገኑበት ምስጋና በግእዙ እንደዚህ ይላል:-

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ፤
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም::
ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ፤
ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ በኵሉ ዓለም::

ቡሩክ አንተ በጽርሐ ቅድሳተ ስብሐቲከ፤
ስቡሕኒ አንተ ወእኩት አንተ ለዓለም::
ቡሩክ አንተ ዘትሬኢ ቀላያተ ነቢረከ ላዕለ ኪሩቤል፤
ስቡሕኒ አንተ ወልዑል አንተ ለዓለም::
ቡሩክ አንተ በዲበ መንበረ መንግሥትከ፤
ስቡሕኒ አንተ ወቡሩክ አንተ ለዓለም::
ቡሩክ አንተ በመልዕልተ ሰማያት፤
ስቡሕኒ አንተ ወክቡር አንተ ለዓለም::

የዚህ ቃለ ውዳሴ ትርጓሜ ከዚህ እንደሚከተለው ይነበባል:-

የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፤
የተመሰገነ ነው÷ ለዘላለሙም የከበረ ነው::
የከበረ የጌትነቱ ስምም ይክበር ይመስገን፤
የተመሰገነ ነው÷ በዓለሙ ሁሉ የከበረ ነው::
ቅዱስ÷ ቅዱስ÷ ቅዱስ ተብለህ በምትመሰገንበት በጽርሐ አርያም አንተ የከበርህ ነህ፤
ለዘላለሙ የተመሰገንህ ነህ::
በኪሩቤል ላይ ሆነህ የውቅያኖስ ጥልቆችን የምታይ አንተ የከበርህ ነህ፤
የተመሰገንህ ነህ÷ ለዘላለሙም የከበርህ ነህ::
በጌትነትህም ዙፋን አንተ የከበርህ ነህ፤
የተመሰገንህ ነህ÷ ለዘላለሙም የከበርህ ነህ::
ከሰማዮች በላይ ባለ ሰማይም የተመሰገንህ ነህ፤
አንተ ለዘላለሙ ፈጽመህ የከበርህ ነህ::
(መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ምዕ. 1÷27-32)

ሠለስቱ ደቂቅ ከወደቁበት ያነሣቸውን፣ ከተጣሉበት የፈለጋቸውንና ከነደደባቸው እቶነ እሳት መልአኩን ልኮ ያዳናቸውንና የታደጋቸውን አምላክ በስድስት አንቀጽ ወስነውና ስድስት ጊዜ መላልሰው



ማመስገናቸው ምሥጢሩ እኛን ከተጣልንበት ከዚህ እሳት ውስጥ ተራዳኢና ታዳጊ የሆነውን መልአክህን ልከህ እንዳዳንከን ሁሉ፤ እንደዚሁም ከስድስት መቶ ዘመን በኋላ፤ አንድም አባታችን አዳም ከወደቀ ከስድስት ሺህ ዘመን በኋላ ይህንኑ ኃያል መልአክ ወደዚህ ዓለም ልከህ፣ በብሥራተ መልአክ ተፀንሰህ፣ ከድንግል ማርያም ተወልደህ፣ ወደ ሲኦል እሳት ወርደው የነበሩ ነፍሳትን ታድናለህ፣ ከመከራ ነፍስም ትታደጋቸዋለህ ሲሉ ነው:: ዳግመኛም በዚህ አምላካዊ ትድግና ከእቶነ እሳት የዳኑት ወጣቶች ሦስት መሆናቸው ምሥጢሩ በወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን አዳም፣ ሔዋንና ልጆቻቸው፤ አንድም ሥጋ፣ ነፍስ፣ ደመ ነፍስ ፈጽመው ለመዳናቸው ምሳሌ ነው::[141]

በዜና አበው ትምህርት ወይም ጥናት [Patrology/ Patristic Studies] እንደምንመለከተው ተላውያነ ሐዋርያት [Apostolic Fathers] የተባሉ ቅዱሳን አበው በተነሡበት ዘመን የነበረውና ለሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የነገረ ማርያም አስተምህሮ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተው ቅዱስ ጀስቲን ሰማዕት [Justin Martyr] እነዚህን ሦስት ወጣቶች “ከክርስቶስ በፊት የነበሩ ክርስቲያኖች” ["Christians before Christ"][142] በማለት ሰይሟቸዋል:: በዚህ አባታዊና ሐዋርያዊ ትምህርቱም በሠለስቱ ደቂቅ ዘመን የተፈጸመው አምላካዊ የቸርነትና የማዳን ሥራ በዘመነ ሐዲስ በብሥራተ መልአክ የሚጀመረውን አምላካዊ የድኅነት ጉዞ እጉልቶ የሚያሳይና የሚያስረዳ አምሳል፣ መርገፍ መሆኑን አስገንዝቦአል::

ልበ አምላክ የተባለው ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊትም ርትዕ ወዓት ወብዙኅ ምሕረት የሆነው አምላክ በሠለስቱ ደቂቅ ያደረገው የቸርነት ሥራና አባታዊ ትድግና በዘመነ ሥጋዌ ከሚፈጸመው ምሥጢረ ድኅነት ጋር የተያያዘ ጥልቅ ምሥጢር እንዳለው ሲያስረዳ:- “አኅለፍከነ ማዕከለ እሳት ወማይ፤ ወአውፃእከነ ውስተ ዕረፍት፤ በሚነድደው

[141] መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፤ ገጽ 316-317:: ትርጓሜ መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ፤ (በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከመጋቢ ብሉይ መዘምር ታዬ የመጻሕፍተ ብሉያትን ትርጓሜ ከተማርኩበት ማስታወሻ የተወሰደ)::
[142] Bettenson, *The Early Christian Fathers*, 60.

እሳትና በሚያሰጥመው ውኃ መካከል በቸርነትህ ከልለህ አሳለፍከን፤ ወደ ዕረፍትም አወጣኸን።» (መዝ. 65÷12) ሲል ተናግሮአል። ቅዱስ ዳዊት ከላይ ከቁጥር 10 ጀምሮ «እስመ አመከርከነ እግዚኦ ወፈተንከነ ከመ ይፈትንዎ ለብሩር። ወአባእከነ ውስተ መሥገርት። ወአምዳእከ ሕማመ ቅድሜነ፤ ወአፅአንከ ሰብአ ዲበ አርእስቲነ» እያለ የመከራውን ጽናትና የችግሩን ብዛት እየዘረዘረ ተናግሮ ከዚህ ሁሉ ፈተና በኋላ የተደረገውን የእግዚአብሔርን አድኅኖት ገልጦ መስክሮአል። ይህ ቃለ ትንቢት በሦስት ዓይነት መንገድ ይተረጎማል። ስለሆነም ሁለቱ ትርጓሜያት እስራኤል ዘሥጋን የተመለከቱ ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ እስራኤል ዘነፍስ የተባሉ ምእመናን ሐዲስን የሚመለከት ነው።[143] ዘርፈ ብዙ የሆነው የዚህ ገጸ ንባብ ትርጓሜ ስልትም ከዚህ እንደሚከተለው ተገልጿል።

በመጀመሪያው ትርጓሜ መሠረት እስራኤል ዘሥጋ ከአገራቸው ከኢየሩሳሌም ተሰደው ወጥተው፣ በእንግድነት በሚኖሩባት በምድረ ግብፅ በባርነት ቀንበር ተይዘው፣ በልዩ ልዩ ዓይነት መከራና ችግር መፈተናቸውን የሚገልጥ ነው። ይኸውም ወርቅንና ብርን ጽርየቱን በእሳት እንዲፈትኑትና እንዲያውቁት፤ እንደዚሁም ሁሉ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሕዝቡን ጽርየተ ሃይማኖት ወምግባር ለማወቅ በልዩ ልዩ ዓይነት መከራ ፈትኗቸዋል። ይህንንም ራሱ ባለቤቱ በነቢዩ በኢሳይያስ አድሮ «እነሆ አንጥሬሃለሁ ነገር ግን እንደ ብር አይደለም፤ በመከራም እቶን ፈትኜሃለሁ።» (ኢሳ. 48÷10) በማለት ተናግሮአል። ሕዝበ እስራኤል ጽኑ የሆነ የመከራ ወጥመድ ወዳለበት ወደ ምድረ ግብፅ በመግባታቸውም ምክንያት በባርነት የገዟቸው ግብፃውያን በላያቸው ላይ ሰልጥነው ይኖሩባቸው ነበር።

በመሆኑም ከመከራው ጽናት፣ ከፈተናው ዓይነትና ከችግሩ ብዛት የተነሣም እስራኤል ወደ ፈጣሪያቸው ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው በጮኹ ጊዜ መሐሪ ወመስተሣህል የሆነው አምላክ በኮሬብ ተራራ ተገልጦ «በግብፅ ያለውን የሕዝቤን መከራ በእውነት አየሁ÷ ከአስገ

(143) *መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ 316-317።*



ባሪዎቻቸውም የተነሣ ጩኸታቸውን ሰማሁ፤ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ፤ ከግብፃውያንም እጅ አድናቸው ዘንድ ከዚያችም አገር ወተትና ማር ወደምታፈስው አገር ወደ ሰፊይቱና ወደ መልካሚቱ አገር ... አመጣቸው ዘንድ ወረድሁ።» (ዘጸ. 3÷7-9) ሲል ተናገረ።

በዚህም ቃለ ተስፋ መሠረት እንደ እሳት ከሚያቃጥለው የግብፅ ባርነት ሕይወት ነጻ አወጣቸው፣ ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ በደረቅ አሻገራቸው። ዳግመኛም መና ከደመና አውርዶ እየመገባቸው፣ ውኃ ከዓለት አፍልቆ እያጠጣቸው «መርሖሙ መዓልተ በደመና ወኵሎ ሌሊተ በብርሃነ እሳት፤ ቀን በደመና መራቸው÷ ሌሊቱንም ሁሉ በእሳት ብርሃን።» (መዝ. 77÷14) እንዲል የቀኑ ዋዕየ ፀሐይ እንዳያቃጥላቸው በዓምደ ደመና ጋርዶና ከልሎ፣ የሌሊቱ ግርማ ጽልመት እንዳይከብድባቸው ደግሞ በዓምደ ብርሃን፣ በዓምደ እሳት እየመራ ወደ ተስፋይቱ አገር ወደ ምድረ ርስት ወደ ከነዓን አግብቷቸዋልና ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ወደ ዕረፍተ ኢየሩሳሌም አወጣኸን በማለት መሰከረ።

ሁለተኛው ትርጓሜ ደግሞ እሥራኤላውያን ገጸ ልቡናቸውን ከእግዚአብሔር ፊት መልሰው በበደሉ ጊዜ ከአገራቸው ከኢየሩሳሌም ተማርከው ወጥተው፣ ወደ ፋርስ ባቢሎን ተሰደው ይኖሩ ነበር። በዚያም ሰባ ዘመን ሙሉ በእንግድነት በኖሩባት በባቢሎን በተለያየ ዓይነት መከራ እንደተፈተኑ ከላይ የጠቀስነው የቅዱስ ዳዊት ቃለ ትንቢት ያስረዳል። ዳግመኛም ወርቅን ብርን በእሳት እንደሚፈትኑትና በዚህም ግብዝነቱ እንዲታወቅ፤ ሕዝበ እሥራኤልም በዔዋዌ (በምርኮ) ወቅት በመከራ ሥጋ ተፈትነዋል። ይህም ይታወቅ ዘንድ በኃጢአታቸውና በበደላቸው ምክንያት በጠላቶቻቸው እጅ ተማርከው አሕዛብ ጽኑ መከራን ወደሚያጸኑባቸው ወደ ባቢሎን ወርደዋል። በዚያም በምርኮ የወሰዷቸው ባቢሎናውያን በእሥራኤላውያን ላይ ሰልጥነውባቸው ይኖሩ ነበር። (መዝ. 136÷1-6)